መግቢያ

ቅድስናና ክብር ሀብታትና ምሥጢራት የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቦች ናቸው።ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው የዚህ ቅድስና እና ክብር ወራሽ እንዲሆን ስለሆነ ይህንን ተረድተው ይህ ሀብትና የምሥጢር ጸጋ በሚገኝበት መንገድ መሰናክሉን ሁሉ አልፈው ከፍጻሜ የደረሱ በክብሩ ክቡራን በቅድስናው ቅዱሳን ተብለው ተጠርተዋል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ቅድስት ነፍሱንና ሥጋውን በፈቃዱ በሞት እንደለየ ሁሉ ከክርስቶስ ፍቅር የተነሣ በፈቃዳቸው ከዓለመ ሥጋና ተድላ ተለይተው ከዚህ ዓለም ሥጋዊ አሠራር አምልጠው ወደ ዓለመ ነፍስ የገቡትንና የመላእክትን ሕይወት በዚህ ዓለም ሁነው የኖሩትን ቅዱሳንን እናከብራቸዋለን።

ይህ ለኦርቶዶክሳውያን እንግዳና አዲስ ትምህርት ባይሆንም ለዚህ ሥልጠና ተሳታፊዎች አስቀድመን ማሳሰብ የምንፈልገው ቅዱሳንን ስናከብር የፈጠረንን፣በአንድነትና በሦስትነት የሚሠለስና የሚቀደስ እግዚአብሔርን፣በቀራኒዮ አደባባይ ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶና ደሙን አፍስሶ ያዳነንን፣ከሦስቱ አካላት አንዱ የሆነውን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ረስተን፣ የእርሱንም ክብር ለቅዱሳን ሰጥተን ሳይሆን አምላካችን ራሱ ያከበራቸውን ማክበራችን የእርሱን ሕግና ትዕዛዝ መፈጸማችን መሆኑን ነው።

ይኸውም፦ “ዘኪያክሙ ተወክፈ ኪያየ ተወክፈ፤ወዘኪያየ ተወክፈ ተወክፎ ለዘፈነወኒ- እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ፣እኔንም የተቀበለ የላከኝን ተቀበለ” ብሎ የወዳጆቹ የቅዱሳንን ባለሟልነት ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮናልና።

ስለዚህ ሠልጣኞች ከዚህ የፍጹምነትና የቅድስና መንገድ አንጻር የራሳቸውን ሕይወት በቃለ እግዚአብሔር መስተዋትነት እየተመለከቱ በቅድስና መንገድ ካለፉና በቅድስና ሕይወት ከኖሩ ቅዱሳን እየተማሩና ክብራቸውን፣የተገባላቸውን ቃል ኪዳን እያስተዋሉ ሥልጠናውን እንዲከታተሉ ያስፈልጋል።በፍጹምነት መንገድ የተጓዙ ቅዱሳን በረድኤታቸው እንዳይለዩንና እንዲራዱን፤ቅዱሳንን ለዚህ ክብር ያበቃ አምላክ ቅዱሳን ቅዱስ እግዚአብሔር እኛንም እንዲረዳን በማመን፣በመማፀንና በመጸለይ ሥልጠናውን በአግባቡ እንድንከታተል ፈቃዱን ከበጐ ፈቃዳችን ጋር ያስማማልን።

የሥልጠናው ዓላማ፡-

አጠቃላይ ዓላማ፡-

መሠረታዊውን የቤተ ክርስቲያን "ነገረ ቅዱሳንን" አስተምህሮ ትውፊቱንና ሥርዓተ አምልኮውን በጠበቀ መልኩ ማስተማር የሚችሉ በተለይም ማኅበሩ በቀረጸው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ለግቢ ጉባዔያት ተማሪዎች ተከታታይ ትምህርት መስጠት የሚችሉ ሰባኪያን ወንጌልን ማፍራት ነው።

ዝርዝር ዓላማ፡-

ሠልጣኞች ከዚህ ሥልጠና በኋላ

1.የነገረ ቅዱሳንን ትርጉም ምንነት ይረዳሉ

2.የነገረ ቅዱሳን ትምህርት ምንጮች ይለያሉ

3.ስለ ነገረ ቅዱሳን መማር ጥቅሙን ያውቃሉ

4.በቅዱሳን ቃል ኪዳን ይጠቀማሉ

5.የቅዱሳን አማረ ፍኖት ይከተላሉ

6.በቅዱሳን ምልጃ ይተማመናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ምዕራፍ አንድ

1.ነገረ ቅዱሳን

1.1. ትርጓሜ፡-

ወደ ነገረ ቅዱሳን ጠቅላላ ትምህርት ከመግባታችን በፊት አንዳንድ ቃላትን ተርጉመን ማለፋችን ትምህርታችንን የጠራና የተረዳ ያደርገዋል "ነገረ ቅዱሳን" የሚለው ስያሜ ሁሉም ቅዱሳን የሚጠሩበት ገኹር የሆነ ጥቅል ስም ነውና።

1.1.1. **ነገር**፡- "ነገር" የሚለው ቃል በቤተ ክርስቲያን አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አጉልቶ ለማሳየት የሚረዳና የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን የሚጠቀሙበት ገላጭ ቃል ነው።ለምሳሌ ነገረ መለኮት፣ነገረ ድኅነት፣ነገረ ማርያም .....እንዲባል።

1.1.2. **ቅዱስ**፡- "ቅዱስ" የሚለው ቃል "ቀደሰ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ነው።ትርጉሙም፡- አመሰገነ፣አከበረ፣ለየ፣መረጠ ማለት ይሆናል።ቅዱስ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ቅዳሺ፣ በሱርስት(የሶሪያ ጥንታዊ ቋንቋ) ቃዲህ፣በዐረብኛ እንደ ግዕዙ ቅዱስ ይባላል።ትርጉሙም ተመሳሳይ ነው።

1.2.የባሕርይና የጸጋ ቅድስና

1.2.1.የባሕርይ ቅድስና፡-

ቅድስና፣ቅዱስ፡-ከሁሉም በላይና ከሁሉም በፊት ይህ ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው (የሚያገለግለው) ለሥራዊት ጌታ ለቅዱስ እግዚአብሔር ነው።ቅዱስነት የባሕርይ ገንዘብነቱ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው።ይህም ማለት ቅድስናው ከእርሱ የማይለይ ከማንም ያልተቀበለውና የማይቀበለው፣ማንም ሊወስድበት የማይችለው፣ለሌላ ሲሰጥም የማይጐድልበትና የማይከፈልበት የራሱ ገንዘብ ብቻ ማለት ነው።ቅድስና እና እግዚአብሔር ተለያይተው ሊነገሩ አይችሉም አይገባምም በእግዚአብሔር ዘንድ ከቅድስና በስተቀር ሌላ ነገር አይታሰብም በቅድስናው ርኩሰት፣በጻድቅነቱ ሐሰት፣በባዕልነቱ ንዴት(ድኅነት) የሌለበት ነውና።

ስለዚህም ሱራፌል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ የተነሣ ተሞልታለች።በማለት የባሕርይ ቅድስናውን በምስጋና ገልጠዋል።ኢሳ6፥3፣ራዕ 4፥8።እግዚአብሔር የባሕርይው መገለጫ ሁኖ የሚጠራበት ስሙም ቅዱስ የሚለው ነው። እግዚአብሔር ከአማልክትና ከክፋት ሁሉ የተለየ የተፈራና የተከበረም ስለሆነ የሚመስለውና የሚተካከለውም የሌለ ብቸኛ ቅዱስ ነው። "እስመ አልቦ ቅዱስ ከመ እግዚአብሔር ወአልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ.....1ሳሙ 2፥2፣"መኑ ይትኤረዩ ለእግዚአብሔር በደመናት ወመኑ ይመስሎ ለእግዚአብሔር እም ደቂቀ አማልክት አኮኑ ስቡሕ በምክረ ቅዱሳን"መዝ 88፥6 ተብሎ ተወድሷል።

1.2.2. <u>የጸጋ ቅድስና</u>

የጸጋ ቅድስና ማለት ከቅዱስ እግዚአብሔር በስጦታ የተሰጠ የተገኘ ማለት ነው።ተደጋግሞ እንደተገለጸው በባሕርዩ ቅዱስ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ የፍጡራን ቅድስና መገኛውና ምንጩ እርሱ ብቻ ነው።ሰው ወይም ማናቸውም ነገር ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሲለይ ቅዱስ ይባላል።ኢያ 6፥19 ሰው ወይም ማናቸውም ነገር ቅዱስ የሚሆነው ከእግዚአብሔር የተነሣና ለእግዚአብሔር የተለየ ስለሚሆን ነው።እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑ ለእግዚአብሔር የሆነ ሁሉ ቅዱስ መሆን አለበት።ዘሌ 19፥2፣1ጴጥ 1፥15።

1.3.<u>ቅዱሳን</u>

ቅዱስ የሚለው ቃል አንድን ነጠላ ነገር የሚያመለክት ሲሆን፣ቅዱሳን የሚለው ደግሞ ብዛትን የሚያመለክት ነው።በዚህ ሥልጠና የምንመለከተውም ነገረ ቅዱሳን ስለሆነ በባሕርዩ ቅዱስ የሆነ እግዚአብሔር በረድኤት ያደረባቸው፣በጸጋ የተዋሃዳቸው፣እግዚአብሔርን በፍጹም ሃይማኖት፣በተቀደሰ ሕይወትና በመልካም ተጋድሎና የአገልግሎት ሕይወት በማገልገል ከራሳቸው አልፈው ለሌላው ሰው በረከት (ጥቅም) የሆኑትን ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ቅዱሳን ብሎ ይጠራቸው ዘንድ አያፍርም "እነ እቄድሰ ርዕስየ ከመ ይኩኑ ቅዱሳን በጽድቅ በእውነት ቅዱሳን እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ"በማለት የሰው ልጅ ቅዱስ ይሆን ዘንድ ራሱን የተቀደሰ መሥዋዕት አድርጎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን በማፍሰስ ቅድስናን እንደሠጠ ተናገረ።ዮሐ 17፥19።

በመሆኑም የቅዱሳን ቅድስና የጸጋ ቅድስና ነው ማለት ነው።ቅዱስ የሚለው ቃል ለእግዚአብሔርም ከሰው ወገን ቅዱሳን ለሆኑም የሚነገርና በቅጽልነት የሚያገለግል ከሆነ እንዴት ተለይቶ ይታወቃል?የሚል ጥያቄ ሊፈጥር ይችል ይሆናል ቅዱስ የሚለው ቃል ደረጃውና መጠኑ የሚታወቀው በሚቀጸልለት ባለቤት ነው እንጂ በቃል ብቻ አይደለም።

- ቅዱስ እግዚአብሔር ስንል የእግዚአብሔር ሁለንተናዊ ነገር
- ከፍጡራን መካከል ቅዱሳን የሆኑትን ቅዱስ ብለን ስንጠራ ተጋድሎውን የአገልግሎቱን ሕይወት የተገባለትን ቃል ኪዳን እናስባለን ማለት ነው።

<u>ለምሳሌ</u>፦ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ።(ዮሐ 8፥12)በማለት ስለ ራሱ ብርሃንነት ተናግሮአል።ደቀ መዛሙርቱንም እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ብሏቸዋል።(ማቴ 5፥14)ብርሃን የሚለው ቃል አንድ ዓይነት ሲሆን በክርስቶስና በደቀ መዛሙርቱ መካከል ያለው ልዩነት ግን የፈጣሪና የፍጡር፣የባሕርይና የጸጋ ተብሎ ይለያል።

ስለዚህ "ቅዱስ፣ብርሃን" የሚሉት ቃላት የሚታወቁት በመልእክታቸውና በክብደታቸው መጠን ነው ማለት ነው።ወንጌላዊው ዮሐንስ የክርስቶስንና የመጥምቁ ዮሐንስን ብርሃንነት ሲያነጻጽር "ወለለሁሰ ኢኮነ ብርሃነ ጻእሙ ዓለ መጽአ ሰማዕተ ይኩን በእንተ ብርሃን-ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ እርሱ (መጥምቁ ዮሐንስ) ብርሃን አልነበረም"።ብሏል ዮሐ 1፥8 ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዮሐንስ መጥምቅ ሲመሰክር "እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ" ብሎ ብርሃንነቱን መስክሮአል።

1.4. <u>ነገረ ቅዱሳን መማር ለምን ያስፈልጋል?</u>

ልዑለ ባሕርይ ቅዱስ እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ አድሮ ሲናገር "ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃም ወደ ወላዶቻችሁም ወደ ሣራ ተመልከቱ አንድ ብቻውን በሆነ ጊዜ ጠራሁት ባረክሁትም አበዛሁትም" (ኢሳ 51፥2)።በማለት በዓይነ ሕሊና ወደ ቅዱሳኑ እንድንመለከት መክሮናል።ወደ ቅዱሳኑ ስንመለከት፦

1.4.1. <u>የእምነት ጽናትን እንማራለን</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።ለሽማግሌዎች የተመሰከረላቸው በዚህ ነውና” በማለት የተመሰከረላቸውን ዋና ዋናዎቹን ስማቸውን፣ማዕረጋቸውንና ግብራቸውን በእምነት ጽናት ተስፋ ያደረጉት ሁሉ እንደተፈጸመላቸው በማስረጃነት ጠቅሷቸዋል።(ዕብ 11፥1-40)።

1.4.2.<u>በረከት እናገኛለን</u>

በረከት በጻድቅ ራስ ላይ ነው፣የጻድቅም መታሰቢያ ለበረከት ነው።ምሳ 10፥6።እንደተባለ ቅዱሳኑን በማክበር በረከት እናገኛለን እግዚአብሔር አብርሃምን .....እባርክሃለሁ፣ስምህንም አከብረዋለሁ፣ለበረከትም ሁን፣የሚባርኩህንም እባርካለሁ፣የሚረግሙህንም እረግማለሁ።ዘፍ 12፥2 በማለት ስሙን የሚያከብሩትን፣በቃል ኪዳኑ የሚታማመኑትን እንደሚባረካቸውና አብርሃምን ለበረከት እንዳደርገው እናስተውላለን።አብርሃምን የመሰሉና በቅድስናና በተጋድሎ በአገልግሎት ጸጋ ከአብርሃም የሚልቁ ቅዱሳን ሁሉ የበረከት ምንጮ ናቸው።

1.4.3.<u>መንፈሳዊ ሕይወት እንማርባቸዋለን</u>።

ቅዱሳን ሕይወታቸው በጸም በጸሎት በስግደት በትሕትና በተስፋ በትዕግሥት እና በአርምሞ በዝምታ የተሞላ ነው።ከእግዚአብሔር ጋር፣ከበጐና ክፉ ሰዎች ጋር በመከራና በደስታ ጊዜ ሕይወታቸውና የኑሮ ፍልስፍናቸው (ዘይቤያቸው) እንዴት እንደ ነበር መማር እንችላለን። “የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውን ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታችሁ ምሰሉአቸው”።ዕብ 13፥7 እንዲል።

1.4.4.<u>የተጋድሎ ውሎአቸውን እንድናውቅ ይረዳናል</u>

አስቀድመን እንደተናገርነው የቅዱሳን ሕይወት በተጋድሎ የተሞላ ነው ጌታችን በወንጌል “በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፣ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ”።ዮሐ 16፥33።በማለት እንደተናገረው በፍጹም እምነትና ትዕግሥት በመከራ መካከል አልፈዋል በሰይፍ ተመትረዋል፣በመጋዝ ተሰንጥቀዋል፣በእሳት ተቃጥለዋል፣ተሰደዋል፣ተርበዋል፣ ተጠምተዋል፣ታርዘዋል።ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ

“ወንድሞች ሆይ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ

ደስታ ቁጠሩት”።ያዕ 1፥2 እንዳለ መከራውን ሁሉ በደስታ ተቀብለውታል የተጋደሉትም እስከ ሞት ድረስ ነው።ራዕ 2፥10።በዚህ ጉዞአቸው ሁሉ በአሸናፊነት የተወጡ የሃይማኖት ጀግኖች ናቸው።

1.4.5. <u>በቃል ኪዳናቸው እንድንጠቀም ያደርገናል</u>

ከዘመነ አበው ጀምሮ የነበሩ ቅዱሳን በእምነታቸውና በአካሄዳቸው በሕይወታቸው ፍጻሜም እግዚአብሔርን ደስ ስለ አሰኙት የተለየ ቃል ኪዳን ተቀብለዋል።ይህም ቃል ኪዳን የሚጠቅመው በእነርሱ ቅድስናና ተጋድሎ የሚያምኑትን፣በምልጃቸውና በጸሎታቸው የሚተማመኑትን ሰዎች ነው።

1.4.6. <u>አሠረ ፍኖታቸውን እንድንከተል</u>

ከእርሻ ሜዳ የተጠራው ነቢዩ ኤልሳዕ እግዚአብሔር ኤልያስን በዐውሎ ነፋስና በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ ሊወስደው በወደደ ጊዜ ኤልያስን ኤልሳዕን፡-እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ልኮኛልና በዚህ ቦታ ቆይ ቢለውም ኤልሳዕ ግን ሕያው እግዚአብሔርን በሕያው ነፍስህ እምልልሃለሁ አልለይህም ነበር ያለው።2ነገ 2፥1 ኤልያስን የተከተለ ኤልሳዕ በረከቱ እጥፍ ሁኖ ስለ አደረበት፡-

- በመጐናጸፊያው የዮርዲያኖስን ወንዝ ከፈለ
- የሞተውን በአካለ ሥጋ እያለና ከሞተ በኋላ ማስነሣት ችሏል
- የመረረውን ውኃ ማጣፈጥ ችሏል
- እህል በጠፋበት ዘመን ማበርከት ችሏል
- በሃይማኖታዊ አቋም ከነገሥታት ጋር ታግሏል

- ሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስ
- ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ
- ኢትዮጲያዊው ሊቅ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ .....ሃይማኖታዊ ጽናታቸው በመከራ ጊዜ ትዕግስታቸው የጸሎት ሕይወታቸው በጥንቃቄ የተሞላ ስብዕናቸውና ክርስቲያናዊ ስነ ምግባራቸው የአገልግሎት ትጋታቸው ዛሬ ላይ ለምናገኘው አቅምና ብርታት ይሆናል የሄዱበትን ፈለግ እንድንከተል ያደርገናል።

1.5.<u>የነገረ ቅዱሳን ትምህርት ምንጮች</u>

ስለ ነገረ ቅዱሳን ልባችንን ሞልተን አፋችንን ከፍተን እንድንናገርና እንድናስተምር የሚያደርጉን ምንጮቻችን የታመኑና ሕያው ምስክሮች ስለሆኑ ነው።

1.5.1.<u>መጽሐፍ ቅዱስ</u>

ከሰዎች መካከል ብቻም ሳይሆን እግዚአብሔርን ከሚያምኑ ሰዎች መካከል የተለዩና የተመረጡ በእግዚአብሔርም ዘንድ ሞገስ ያላቸው ቅዱሳን እንደነበሩ የማይለወጠውና የማይናወጠው መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጠኝነት ይነግረናል።

አምላካችን ቅዱስ እግዚአብሔር በሥርዓተ አምልኮ ውስጥ ተደብቀው በቅዱሳኑ ላይ ክፉ ያደረጉትን ሲወቅስ፦

"እናንተ እባቦች የእፉኝት ልጆች ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ?እነሆ ነቢያትንና ጥበበኞችን .....ወደ እናንተ እልካለሁና፣ከእነርሱም ትገድላለችሁ፣ ትሰቅሉማላችሁ፣ከእነርሱም በምኩራባችሁ ትገርፋላችሁ፣ከከተማ ወደ ከተማም ታሳድዳላችሁ፣ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዮ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችኋል።"ማቴ 23፥33-35 በማለት ጠቅለል አድርጎ ጻድቃን ቅዱሳን.....ብለን እንድንጠራና እንድናከብር እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የአፋ እስትንፋስ በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ አስተምሮናል።በተጨማሪም፦

- ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም ማቴ 13፥11።
- ጻድቃን በአባታችው በእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ ማቴ 13፥13
- በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራዕይ እገለጽለታለሁ ወይም በሕልም አናግረዋለሁ ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው፤ እኔ አፍ ለአፍ በግልጽ እናገራዋለሁ ዘኁ 12፥6 በማለት እግዚአብሔር ተናግሮአልና።

1.5.2. <u>ቅዱሳን ገድላት</u>

በመሠረቱ ገድል ስንል የቅዱሳን ዜና ተጋድሎ፣የሕይወት ታሪካቸው ማለት ነው። <u>ለምሳሌ</u>፡-ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ገድል ሲናገር፡-በመሥዋዕት እንደሚደረግ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፤የምሄድበት ጊዜ ደርሷል፤መልካሙን ገድል ተጋድያለሁና ሩጫዬን ጨርሻለሁ፤

ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ 2ጢሞ 4፡6 ብሎ የተናገረው ገድለ ቅዱስ ጳውሎስ ይባላል ይህም ማለት፡-

- ቅዱስ ጳውሎስ መቼ ተሠዋ?
- ቅዱስ ጳውሎስን የሰዋው ማን ነው?
- የተሠዋው በምንድነው?
- እንዴት ተሠዋ በየት አገር የሚለውን አጠቃሎ የሚይዝ ነው።

በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ "የሐዋርያት ሥራ-ግብረ ሐዋርያት" እያልን የምንጠራው በሌላ አጠራር ገድለ ሐዋርያት ዜና ሐዋርያት ይባላል። "ገድለ ሐዋርያት፣ገድለ አርድዕት" የሚባሉ ራሳቸውን የቻሉ ስለ ቅዱሳን ሐዋርያትና አርድዕት ተጋድሎ አገልግሎት፣ሕይወት የሚናገር መጽሐፍም በጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ይገኛል።እነዚህ መጻሕፍት (ገድላት) መጽሐፍ ቅዱስን መነሻ አድርገው እግዚአብሔርን እንዴት እንደ አገለገሉ፣ሕይወታቸው እንዴትና በምን እንደተደመደመ የሚነግሩን መጻሕፍት ናቸው ።

1.5.3. <u>ቅዱሳት መካናት</u>

ቅዱሳት መካናት ማለት ቅዱሳኑ የተወለዱበት፣በጸም በጸሎት ያሳለፉበት፣መከራ የተቀበሉበት፣ የከበረ አጽማቸው ያረፈበት፣ቃል ኪዳን የተቀበሉበት ማለታችን ነው።ከዚሁ ጋር በዚህ ቅዱስ ቦታ፡-

- በስማቸው የፈለቀው ጸበል
- የጸለዩበትና ፈውስ የሚሰጠው አፈር (እምነት)
- መካነ መቃብራቸው
- ቅዱሳት ሥዕሎቻቸው

- በቅርስነት የተቀመጡ ልብሶቻቸው፣ መቋሚያቸው፣ መስቀላቸው ዛሬም ድረስ የቅዱሳኑን ቅድስናና ሕያውነት በምስክርነት ይናገራል።ለምሳሌ ደብረ ሊባኖስ፣አቡነ ሐራ ገዳም፣ አቡነ መልከ ጼዴቅ.....።

1.6. የቅድስና ሕይወት መሠረት ምንድነው?

ልዑለ ባሕርይ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን የስሙ ቀዳሽ የክብሩ ወራሽ ይሆን ዘንድ በአርዓያውና በአምሳሉ ግሩምና ድንቅ አድርጐ በመፍጠር በገነት አኖረው የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ቅድስና መጠበቅ ባለመቻሉም ከገነት ተባረረ።

- ከዓለመ መላእክት ወደ ዓለመ እንስሳት ወረደ መዝ 48÷12እና 20
- እኩያት ፍትወታትም በሕይወቱ ስለጠኑበት
- በባሕርያቸው አማልክት ያልሆኑትን በማምለክ ተገዛ ገላ 4÷8
- አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት በእግረ አጋንንት ተረገጠ
- በሥጋው ወደ መቃብር በነፍሱ ወደ ሲኦል ተጋዘ

ከዚህ የሞት ጕዳና ሊያወጣና ወደ ትክክለኛው መንገድ ሊመራ የመጣው መድኅን ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ “አነ ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት የጽድቅና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ”።በማለት የተቅበዘበዘውን የሰው ዘር ወደ ሕይወቱ የሚመልስና የሕይወትን መንገድ የሚያሳይ መሆኑን ተናገረ።ዮሐ 14÷6።

አንዳንዶች ባለማወቅ “ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም” የሚለውን ያለ ቦታው በመተርጐም <u>ለምልጃ የተነገረ አስመስለው ይጠቅሳሉ</u>።በመሠረቱ “አይክል መጺአ ኃቤየ እመ ኢስሀበ አብ የላከኝ አብ ከሳበው በስተቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም”።ዮሐ 6÷44 በማለት ቅዱስ ወንጌል ይናገራል።ታዲያ በዚህ ክፍለ ንባብ መሠረት እንደ እነርሱ አባባል ከሆነ አብም ወደ ወልድ ያማልዳል ሊባል ነውን? ይህ በፍጹም ስህተት ነው።የሁለቱም ገጸ ንባብ አንድ አይነት መሆኑን ልብ ማለት ይገባል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጽድቅና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ በማለት የተናገረው ስለ ሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

1.በአዳምና በሔዋን ኃጢአት ምክንያት ተዘግታ ኪሩቤልና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ ሲጠብቋት የኖረችውን የገነት በር ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ ክቡር ደሙን አፍስሶ የሚከፍትልን ስለሆነ።

2. የእርሱን የአብ የባሕርይ ልጅነት ስንረዳና ስናምን የአባቱን የባሕርይ አባትነት የምናምንና የምናውቅ ስለሆነ። “እኔን ያየ አብን አይቷል” በማለት እንደ አስተማረ።

3.በኦሪት ተሰውሮ የነበረውን አንድነትና የሦስትነት ምሥጢር የገለጠና ያስተማረ ስለሆነ

4.በዚህች ምድር በሥጋ በኖረባቸው ዓመታት የቤዛነት ሥራ ከመሥራቱ ጋር እኛ ልንሠራው የሚገባንን ሥራና ልንሄድበት የሚገባንን መንገድ በቃልና በተግባር ስለ አሳየን።ለምሳሌ፡-

ብፅዕና የሚያሰጡ መንገዶች አንቀጸ ብፁአን ማቴ 5፥3፣ዮሐ 13፥17።

ጠላቶቻችሁን ውደዱ ብሎ እንዳስተማረ ይሁዳንና የሰቀሉትን መታገሡና ስለ እነርሱም መጸለዩ።ሉቃ 23፥34።

ቀኝ ፊትህን በጥፊ ቢመታህ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት ብሎ እንዳስተማረ “ተነበይ ለነ ክርስቶስ መኑ ጸፍአከ - ክርስቶስ ሆይ ትንቢት ተናገር በጥፊ የሚመታህ ማን ነው” እያለ ሲዘብቱበትና ሲመቱት ሁሉን ማድረግ ሲቻለው በትዕግሥት መቀበሉ፤

ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራም ሲቀበል አልዛተም 1ጴጥ 2፥21።እነዚህ ለምሳሌነት ተጠቀሱ እንጂ ክርስቶስ የሠራው ሥራ በአጠቃላይ ለቤዛነትና ለአርአያነት ነው።ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏል በማለት ፍለጋውን እንከተል ዘንድ አርአያውን በቃልና በተግባር ትቶልን እንደሄደ አስረድቶአል።

አንዳንዶች “ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ” የሚለውንና “ጽድቃችን እንደ መርገም ጨርቅ ሆነ” በማለት ኢሳይያስና ቅዱስ ጳውሎስ የተናገሩትን ሮሜ 3፥11፣ ኢሳ 64፥6። በመያዝ በመጥቀስ ጻድቅ የሚባል የለም በማለት ለመደምደም ይሞክራሉ “ጻድቅ” የለም ተብሎ የተነገረበት ዋና ምክንያት፡-

- ጻድቃን ቢኖሩም የተዘጋውን ገነት ማስከፈት አለመቻላቸውን

- በራሳቸውም ጽድቅ ገነት መግባት አለመቻላቸው
- የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤን ተስፋ ማድረጋቸውን ይገልጻል እንጂ ጻድቃን እንደነበሩማ ምስክሩና መምህሩ ባለቤቱ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል።ማቴ 23፥34፣ማቴ 13፥17።

በአዲስ ኪዳን ደግሞ "ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው።አሮጌው አልፏል፥ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል።"2ቆሮ 8፥17

- ክርስቶስን በመከራው ብንመስለው በክብር እንመስለዋለን።ሮሜ 8፥17
- ብንጸና ከእርሱ ጋር እንነግሣለን።2ጢሞ 2፥12
- ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።በማለት የቅዱሳንን ክብር ከፍ አድርጐታል።ራዕ 3፥21

1.7. <u>የቅዱሳን ጥሪ</u>

የቅድስና ጥሪ ለሰው ዘር በሙሉ የተላለፈ ቢሆንም ማቴ 5፥3-11 "የተጠሩ ብዙዎች ናቸው የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው" እንደተባለው የፈጣሪያቸውን የቅድስና ጥሪ የተቀበሉና በዚህ ሕይወት ጸንተው የኖሩ ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

ቅዱሳን የተጠሩበት መንገድ፡-

- ሙሴ፣ዳዊት፣አሞጽ ከእረኝነት
- ኤልሳዕ ከእርሻ ቦታው
- ዮሐንስ፣ያዕቆብ፣ጴጥሮስ ከዓሣ አጥማጅነት
- ማቴዎስ ገንዘብ ሰብሳቢነት (ቀራጭነት)
- ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ከማሳደድ
- የመነኮሳት አባት እንጦንስ ከቤተ መቅደስ ማቴ 19፥21
- ስምኦን ዘዓምድ በቅዳሴ ጊዜ ማቴ 16፥26
- ርዕሰ ባሕታውያን ጳውሊ ወደ ቀብር ከሚወሰድ ባለፀጋ
- አብርሃም መርዓዊ ከሙሽርነት (ከጫጉላ ቤት) በብርሃን እየተመራ

- አባ ብሰይ መልአከ እግዚአብሔር መጥቶ “ከልጆችሽ አንዱን ስጪኝ” ይልሻል እግዚአብሔር ብሎ ለእናቱ ሲነግራት እናትየዋ ሁሉም የእርሱ ናቸው የወደደውን መርጦ ይውሰድ አለችው መልዓኩ አባ ብሰይን መርጦ ወሰደ።
- ሙሴ ጸሊም ከሽፍታነት

እግዚአብሔር ቅዱሳኑን የሚጠራበት መንገድ ብዙ ነው።ክቡር ዳዊት እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ማን ነው በሚመርጠው መንገድ ያስተምረዋል እንዳለ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ሲጠራቸው ጥሪውን ተቀብለው በተግባር ፈጽመዋል።

1.8. <u>የእግዚአብሔር ምርጫ</u>

እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ አስተካክሎ የሚወድ የፍቅር አምላክ ነው።

ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው የሚሰጥ ፈታሒበርትዕ ኰናኒ በጽድቅም ነው።በእግዚአብሔር ዘንድ አድልዎ የሚባል ነገር የለም ነገር ግን የማያደላ ከሆነ አንዳንዶቹን መርጦ ክቡራን፣ጻድቃን፣ቅዱሳን .....ለምን አደረገ የሚል ጥያቄ ሁልጊዜ ሰዎች ሲያነሱ ይሰማሉ ከሚያነሷቸው ጥቅሶች መካከልም

1. ተነከሩ ኃጥአን እማሕፀን -ኃጥአን ከማሕፀን ጀምረው ተለዩ መክ 57፥3 በመያዝ ኃጥአን ገና ሳይወለዱ በማሕፀን ተወስኖባቸዋል።

2. ርብቃ ከወለደቻቸው ልጆች “ያዕቆብን ወደድኩ ኤሳውን ግን ጠላሁ” ሮሜ 9፥10 የሚለው ነው።ይህ ማለት በማሕፀን መወሰኑን ሳይሆን የሚያመለክተን እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆነውን ነገር እንደሆነና እንደተፈጸመ አድርጐ ማወቁን የሚያሳይ ነው እንጂ አስቀድሞ መወሰኑን አይደለም።ለዚህም የያዕቆብና የኤሳውን የሕይወት ፍጻሜ መመልከት ይቻላል። ዘፍ 25፥27-34፣ዘፍ 28፥1-9፣ዕብ 12፥16፣ዘፍ26፥35።ለምሳሌ አንድ ሐኪም በሽተኛውን መርምሮ እንደማይድን ቢናገር መሞቱን አወቀ እንጂ ሐኪም በሽተኛውን ገደለው እንደማይባለው የእግዚአብሔር አሳብም ከዚህ የተለየ አይደለም።

ምዕራፍ ሁለት

ቅዱሳን እነማን ናቸው?

2.1.ቅዱሳን ሰዎች

ቅዱሳን ሰዎች ለተለያየ ተግባር ነገር ግን ለአንድ ዓላማ በእግዚአብሔር የተጠሩ ናቸው። መጠራት ብቻም ሳይሆን ከተጠሩት መካከልም ተለይተው የተመረጡ ናቸው።ይህንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን

- ✓ አስቀድሞ ሐዋርያትን
- ✓ ሁለተኛም ነቢያትን
- ✓ ሦስተኛም አስተማሪዎችን
- ✓ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን
- ✓ ቀጥሎም የመፈወስ ስጦታ ያላቸውን አድርጓል በማለት ተናግሯአል።

በመሆኑም እግዚአብሔር የልጁን መልክ እንዲመስሉ ወስኖ የጠራቸውን፣ያጸደቃቸውንና ያከበራቸውን ቅዱሳኑን ሁሉ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

2.1.1. ቅዱሳን ነቢያት

ሀብተ ትንቢት ከእግዚአብሔር ተሰጥቷቸው ወደፊት የሚሆነውን ሁሉ በእግዚአብሔር መሪነት በእርግጠኝነት የተናገሩ ናቸው።ነቢያት ሲናገሩም "ከመዝይቤ እግዚአብሔር እግዚአብሔር እንዲህ ይላል……." እያሉ ነው።1ሳሙ 9÷6፣አሞ1÷3፣ሚክ3÷8 የሚናገሩት ነገርም የሚገለጥላቸው፦

በሕልም
በራዕይ } ዘኁ 12÷6
በመልዓክ በኩል ነው } ዳን 10÷11

ነቢያት ትንቢት ከመናገር ጋር ሕዝቡን ይመክሩ ያስተምሩና ይገሥጹ ነበር ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን በመጀመሪያ እወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና።ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተመርተው ተናገሩ ብሏል።2ጴጥ 1÷21።

2.1.2. <u>ቅዱሳን ሐዋርያት</u>

በነቢያት የተነገረው ቃለ ትንቢት መድረሱንና በዘመናቸው መፈጸሙን ለዓለም እንዲመሰክሩና እንዲያስተምሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ተከተሉኝ" ብሎ የጠራቸውና የመረጣቸው ናቸው።ይህም ይታወቅ ዘንድ "ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር የማወቅ ሥልጣን ተሰጥቷችኋል።ብሏቸዋል።ማቴ 13÷10 ከዚሁ ጋር

- ✓ አጋንንትን እንዲያስወጡ } ማር10÷1
- ✓ ደዌንና ሕማምን ሁሉ እንዲፈውሱ }
- ✓ የማሰርና የመፍታት ሥልጣን ማቴ 16÷19
- ✓ ኃጢአትን ይቅር የማለትና የማሥተሰርይ ዮሐ 20÷23
- ✓ የምዕመናንም ሕይወት በአደራነት አስረክቧቸዋል።ዮሐ 21÷15

2.1.3. <u>ቅዱሳን ጻድቃን</u>

ቅዱሳን ጻድቃን የሚባሉት መላ ዘመናቸውን ከጣዕመ ዓለምና ከተድላ ዓለም ተለይተው፡-

- ቤት ልሥራ ዘር ልዝራ ያላሉ
- ፈቃደ ሥጋቸውን ለፈቃደ ነፍሳቸው ያስገዙ
- በጸምና በጸሎት፣በስግደትና በምናኔ ጸንተው የኖሩ
- ድምፅ አራዊትን ጸብአ አጋንንትን ግርማ ሌሊቱን የታገሡ
- ድንጋይ ተንተርሰው ደዋ ጥሰው ጤዛ ልሰው የኖሩ ናቸው።

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እነዚህ ሲገልጽ "ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ቆዳ ለብሰው ዞሩ፤ዓለም አልተገባቸውና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና

በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ" ብሏል።ዕብ 11፥37 ሐዋርያው ዮሐንስም "እርሱ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ጻድቅ ነው። ብሏል ዮሐ 3፥7።

2.1.4.<u>ቅዱሳን ሰማዕታት</u>

ቅዱሳን ሰማዕታት የሚባሉት እግዚአብሔርን ካዱ፣ለጣኦት ሰገዱ ሲባሉ እግዚአብሔርን አንክድም፣ለጣኦትም አንሰግድም በማለት በአላውያን ነገሥታት ፊት ቀርበው ሳያፍሩና ሳይፈሩ ስለ አምላካቸው ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰከሩ የእምነት አርበኞች ናቸው።ሰማዕታት የተቀበሉት የመከራ ዓይነት

- ደማቸውን አፍስሰዋል
- አጥንታቸውን ከስክሰዋል
- በእሳት ነበልባል ተቃጥለዋል
- በሰይፍ ተመትረዋል
- በመጋዝ ተተርትረዋል፣ተሰንጥቀዋል
- በፈላ ውኃ ውስጥ ተቀቅለዋል
- በመንኩራኩርም ተፈጭተዋል
- እንደ ከብት በሕይወት እያሉ ቆዳቸው ተገፍፏል
- ጥፍራቸው ተነቅሏል ጣቶቻቸው ተቀንጥሷል፣ጥርሳቸው ተሰብሯል፣ይህንንም

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጽ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ በወኅኒ ተፈተኑ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ።ዕብ 11፥35 በማለት ነው።በራሱም ላይ የደረሰውን በ2ቆሮ 11፥23፣ሐዋ 14፥29 ተጽፎ እናነብባለን።ይህንን ሁሉ መከራ ተቀብለው ከእምነታቸው እንዳላናወጣቸው ሲገልጽ "ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?መከራ ወይስ ጭንቀት?ወይስ ስደት?ወይስ ረኃብ?ወይስ ራቁትነት?ወይስ ፍርኃት?ወይስ ሰይፍ ነውን?ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጐች ተቆጠርን ተብሎ እንደተጻፈው ነው"።ብሏል ሮሜ 8፥35።

2.1.5.ቅዱሳን አበው

ቅዱሳን አበው የምንላቸው መጻሕፍት ሳይኖራቸው መምህራን ሳይላኩላቸው በሕገ ልቦና ብቻ በቃል (በትውፊት) የተላለፈላቸውን በመያዝ በሥነ ፍጥረት በኩል በመመርመር ፈጣሪያቸውን አምነው እርሱ የሚወደውን ሥራ የሠሩና በአካባቢያቸው በነበረው ጣኦት አምልኮ የኃጢአት ብዛትና ዓይነት ራሳቸውን ያላረከሱ ሰዎች ነው።ለአብነትም ያህል፡-የጽድቅ ሰባኪ የነበረው ኖኅን 2ጴጥ 2፥5።አበ ብዙኀንን አብርሃምን መጥቀስ ይቻላል።ኩፋሌ 10፥42፣11፥1።

2.1.6. ቅዱሳን ነገሥታት

ነገሥታት በሥልጣናቸው በሀብታቸውና በሠራዊታቸው ብዛት ሳይመኩ ሃይማኖት ይዘው ምግባር ሠርተው አገር መርተው የተገኙ ናቸው።ትምክህታቸውም እግዚአብሔር ብቻ ነበር መዝ 19፥7፣117፥6-12።

ነገሥታት ስለ ሃይማኖታቸው ከመጋደላቸውም በላይ የሚመሩትን ሕዝብ ፍርድ ሳያጓድሉ ለሰው ፊት ሳያደሉ ድሀ ሳይበድሉ ጉቦ ሳይቀበሉ በቅንነትና በትሕትና አስተዳድረዋል። አንዳንዶቹም በምናኔ ከዚህ ዓለም በመለየት እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ከአጋንንት ጋር ተጋድለዋል።በገድል ተቀጥቅጠዋል ለምሳሌ ዓጼ ካሌብ፣አብርሃና አጽብሃ፣ቅዱስ ላሊበላ ይምርሃነ ክርስቶስ ይጠቅሳሉ።

2.1.7.ቅዱሳን ሊቃውንት

ቅዱሳን ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጻፍና በመተርጎም፣መናፍቃንን በመከራከርና በመርታት፣ሃይማኖት እንዳይጠፋ፣ክህደት እንዳይስፋፋ፣ትምህርተ ሃይማኖት እንዳይከፋፈል፣ደቀ መዛሙርቱን በማስተማር እና በመተካት ሌሊት ከቀን ያለ ዕረፍት የደከሙ የቤተ ክርስቲያን ጠበቃዎች ናቸው።ይህንንም ሲያደርጉ እስራቱ፣ስደቱ፣ግርፋቱ፣እንግልቱ አልቀረላቸውም።ለምሳሌ፡-

- ቅዱስ ፓሊካርፐስ
- ቅዱስ ሄራኔዎስ
- ቅዱስ አትናቴዎስ
- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወረቅ ተጠቃሾች ናቸው።

2.1.8.ቅዱሳን ጳጳሳት

"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ከሄድኩ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኖች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀ መዛሙርትም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሱ እኔ አውቃለሁ ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሰጽ እንዳላቋረጥኩ ትጉ።"ሐዋ 20፥28። በተባለው መሠረት፡- የካህናትና የምዕመናን

- የሰማያውያንና የምድራውያን ኅብረት አንድነት የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት መርተዋል።የቤተ ክርስቲያን ጠላት ከሆኑ ከአሕዛብና ከመናፍቃን ጋር ታግለዋል።

በአጠቃላይ ጳጳሳት፣መነኮሳት፣ቀሳውስት፣ዲያቆናት፣ምዕመናን እሳት እየነደደባቸው ጽኑ መከራ እየተቀበሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀዋል።ቅዱሳን ለቅድስና የተወለዱት መከራና ፈተና በበዛበት አገልግሎት ውስጥ ነው።

2.2.የቅዱሳን ሰዎች አሳያየም

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ የቅዱሳን አሰያየም በድምፅ ብልጫ አይደለም (ይህ አገላለጥ ፓትርያርክ፣ጳጳሳት ተብለው የሚመረጡትን አይመለከትም ወይም አይወክልም) ቅዱሳንን ቅዱስ የሚያሰኛቸው ሕይወታቸው ነው።ስለ ቅዱሳን ቅድስና እና ጽድቅም ምስክርነት የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው።

ለምሳሌ ኖኅ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ እንደነበር ሲመሰክር "ኖኅም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበር ኖኅ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ"ይላል። ዘፍ 6፥9።

- ካህኑ ዘካርያስና ቅድስት ኤልሳቤጥም “ሁለቱም በእግዚአብሔር በጌታ ትዕዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ የሚሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ”ተብሎ ተመስክሮላቸዋል። ሉቃ 1፥6።

አንዳንዶቹንም ግና በእናታቸው ማሕፀን ሳለ ቅዱሳን እንዳደረጋቸው እግዚአብሔር ሲናገር፦የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ “በሆድ ሳልሠራህ አውቃለሁ፤ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፤ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ” ብሎ ኤርምያስን አናግሮታል።ኤር 1፥4።

ስለ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ የተነገረውም “እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም።ማቴ 11፥11።የሚለው የሚያመለክተው የቅድስናውን ታላቅነት ነው።ቅዱስ ገብርኤልም ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላ ይሆንልሃል።በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል።በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና ገናም በእናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል በማለት መስክሮለታል።

ሱናማዊቷ ሴትም ስለ ነቢዩ ኤልሳዕ ስትናገር ይህ በእኛ ዘንድ ሁል ጊዜ የሚያልፈው ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆነ አውቃለሁ ብላለች።2ነገ 4፥9።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ቅዱሳንን ቅዱስ፣ጻድቅ፣ ሰማዕት በማለት ትሰይማለች።መሥፈርት የሚደረገውም፦

1.እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን ራዕ 2፥10 በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት የተለያዩ ተጋድሎዎችን በመቀበል በጾም በጸሎት ተወስነው በተዋህዶ ሃይማኖት በመጽናት አምልኮተ እግዚአብሔርን በትክክል ፈጽመው ያለፍትንና የተመሰከረላቸውን

2.በጌታችንና በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተመሠረተችውን ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት አምልኮ ጠብቀው በማስጠበቅ በአገልግሎት የተጉትንና የተጋደሉትን

3.የእግዚአብሔርን ቃል ንባቡን፣ትርጓሜውን፣ምሥጢሩን ሳያፋልሱ በማስተማር ምዕመናንን በሃይማኖት ያጸኑትን ክርስትናን ያስፋፉትን አማንያንን ያበዙትን

4.በሃይማኖት ነቀፌታ፣በሕይወታቸው ነውር ያልተገኘባቸው

5.ከዓለም በመለየት በበረሃ ወድቀው ደንጊያ ተንተርሰው፣ጤዛ ልሰው፣ዳዋ ጥሰው፣ዋሻ ዘግተው፣ በበዓት ተከተው፣ጸብዓ አጋንንትን፣ድምፅ አራዊትን ታግሠው ግርማ ሌሊቱን፣የቀኑን ሐሩር፣የሌሊቱን ቁር በመታገሥ ሳይሰቀቁ የኖሩትን፣ስለ ሃይማኖታቸው በመመስከር ያለፍትን

6.ምትሐት ያይደለ እውነተኛ ተአምር በማድረግ የሚታወቁትን፣በአጠቃላይ ከፍጹምነት ማዕረግ የደረሱትን ቅዱሳን እግዚአብሔር በአከበራቸው መጠን ታከብራቸዋለች፣ቅዱስ ብላ በመሰየም በቅድስና ትጠራቸዋለች።ተአምራቸውን ገድላቸውን ትጽፍላቸዋለች።ለጸሎት ለልመና ለምስጋና የሚሆን መልክዕ ትደርስላቸዋለች።የሚታሰቡበትን ዕለትም ታሳውቃለች የመታሰቢያ ዕለታቸውም፡-

1.በልደት ቀናቸው

2.ድንቅ ተአምራት በአደረጉበትና በተደረገላቸው ዕለት

3.ቃል ኪዳን በተቀበሉበት ዕለት

4.በዕረፍታቸው ቀን ከእነዚህ በአንዱ ወይም በሁለቱ ሊሆን ይችላል።

ከዚሁ ጋር በስማቸው ጽላት ይቀረጻል፣የመታሰቢያ ሥዕል ይሳልላቸዋል፣ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ይሠራላቸዋል፣ምዕመናን በክረስትና ስም፣በመጠሪያ ስም እንዲጠሩቱ ታደርጋለች።በዚህም በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረውን 56፥3 ተግባራዊ ታደርጋለች ማለት ነው።

2.3. <u>የቅዱሳን ተጋድሎ</u>

ቅዱሳን በዘመናቸው ሁሉ ከዲያብሎስና በዲያብሎስ በኩል ከሚመጣው ኃጢአት ጋር በማያቋርጥ ጽኑ ጦርነት የኖሩ ናቸው።ይህንን ጦርነት ለማሸነፍና በድል አድራጊነት ለመወጣት ብዙ መከራ ተቀብለዋል።ተጋድሎ የሚባለውም በዘመናቸው ሁሉ ከርኩሳን አጋንንት መናፍስት ከእኩያት ፍትወታት ጋር ያደረጉት መንፈሳዊ ጦርነት ነው።

በቅዱሳንና በአጋንንት መካከል ያለውን ጦርነት ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር መጋደላችን ከሥጋና ከደም ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚሁም ከጨለማ ዓለም

ግዥዎች ጋር በሰማይም ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ ብሏል።ኤፌ 6፥12።ቅዱሳን የተጋደሉት ተጋድሎ በዓይነት ብዙ ቢሆንም ለአብነት ያህል የተወሰኑትን እንጠቅሳለን።

2.3.1.<u>ከፈቃደ ሥጋቸው</u>

በመንፈሳዊ ሕይወት ትልቁ ገድል ከፈቃደ ሥጋ ጋር የሚደረገው ትግል ነው።ፈቃደ ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ ለማስገዛት የሚደረገው ተጋድሎ።ገላ 5፥16።ቅዱሳን የመንፈስን ፍሬ ለመያዝ ሥጋቸውን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ ተብሎ ተነግሮላቸዋል።ገላ 5፥24።አብርሃም ከአገሩ የወጣው ከዘመዶቹ የተለየው ፈቃደ ሥጋውን አሸንፎ ነው።ዮሴፍ የጌታው ሚስት ያቀረበችለትን የዝሙት ግብዣ ማለፍ የቻለው ፈቃደ ሥጋውን ማሸለፍ በመቻሉ ነው ።የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ከቤተ መንግሥት ወጥቶ የሄደውና መከራ የተቀበለው ፈቃደ ሥጋውን አሸንፎ ነው።እነ ዳንኤል በምርኮ ጊዜ የተለያዩ መከራዎችን በፈቃዳቸውና ተገደው መቀበል የቻሉት የሥጋ ምኞትን ማሸነፍ በመቻላቸው ነው።በአጠቃላይ ቅዱሳኑ ሁሉ ነገረ መስቀሉን በማየት ዓለምን ጠልተው እግዚአብሔርን መከተላቸው ቃሉ ከእነሱ ሕይወት ጋር እንዲዋሃድና እንዲስማማ በመፍቀዳቸው ነው።ማቴ 16፥24፣ገላ6፥14 ይህንንም በማድረግ።

ሀ.<u>ከተድላ ሥጋ ርቀዋል (ሸሽተዋል)</u>

ምኞቱን እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ እንደተባለ ቅዱሳን ለዚህ ዓለም ከሚመችና በዚህ ዓለም ከሚገኝ ተድላና ደስታ የራቁ ናቸው።እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ።ሮሜ 8፥12 የሚለው ትምህርት በልባቸው ታትሟልና።

ለ.<u>በመከራ መኖር</u>

ቅዱሳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ ለመካፈል በራሳቸው ላይ ብዙ ጭንቅ መከራን ያመጡ ነበር።ቅዱስ ጴጥሮስ “ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሴት እያደረጋችሁ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ” በማለት እንደተናገረው ከመከራው በኋላ ያለውን ጸጋና ክብር በማሰብ መከራውን ደስ እያላቸው ይቀበሉ ነበር።1ጴጥ 4፥13።

ሐ.በትጋሃ ሌሊት ማሳለፍ

ሁልጊዜ በጸሎት ተግቶ መኖር እንደሚገባ “ጌታችሁ በምን ሰዓት እንደሚመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ” እንደተባለ በመዓልት ብቻ ሳይሆን በሌሊትም በትጋት ሁነው ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ለመኖር ከባሕርይ ድካም፣ከእንቅልፍ፣ከአጋንንትና ከልዩ ልዩ ፈተናዎች ጋር ታግለዋል።ትጋሃ ሌሊት ከባድ ተጋድሎን የሚጠይቅ ነው።

መ.ዕቂበ ሕዋሳት

ማንኛውም ሰው የጽድቅም ሆነ የኃጢአት ሥራ የሚሠራው በሕዋሳቶቹ አማካይነት ነው። ሕዋሳት ሰው ከሌላው ውጫዊ አካል ጋር የሚገናኝባቸው የመረጃ መስመሮች ናቸው።ስለዚህ ሕዋሳት በየክፍላቸው የሚሠሩትን ዓይን የሚያየውን ጆሮ የሚሠማውን አንደበት የሚናገረውን እጅ የሚዳስሰውን መጠበቅ ሕይወትን ይጠብቃል።ኢዮብ 31፥1፣መዝ 38፥1፣ማቴ 18፥18 ቅዱሳን ይህንና ይህን የመሰለውን ተግባራዊ አድርገዋል።

ሠ.መንኖ ጥሪት

መንኖ ጥሪት ማለት በዚህ ዓለም ያለውን ማንኛውንም ሀብትና ንብረት ንቆ መተው ማለት ነው። “ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።”ሉቃ 14፥33 የተባለውን አምላካዊ ቃል ተግባራዊ ያደረጉ ብዙ ቅዱሳን አሉ።

ረ.ትሕትና (ራስን ዝቅ ማድረግ)

ትሕትና ማለት ምግባርና ትሩፋት እየሠሩ ሕግ እግዚአብሔርን እየፈጸሙ ነገር ግን “የማልጠቅምና ከሁሉ የማንስ ነኝ” ብሎ ራስን ዝቅ ማድረግ ነው።አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳልና ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል በማለት ሲናገር ራስን ማክበር የውርደት ራስን ማዋረድ ደግሞ የክብር መሠረት መሆኑን እንረዳለን እርሱ አምላክ ሲሆን በተግባርም

- በባሪያው እጅ ተጠመቀ
- የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ
- በፍጡራኑ ተሰደበ ተደበደበ ይህን ሁሉ አድርጎ ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና በማለት ትሕትናን አስተማረ

- ትሕትና ራስን መንቀፍና መናቅ ነው።ኢዮብ 40፥4፣42፥6
- እኔ አፈርና አመድ ነኝ ዘፍ18፥27
- እኔ ጭንጋፍ ከሐዋርያትም የማንስ ነኝ 1ቆሮ15፥8
- ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ ሉቃ5፥8

ሰ.አፍቅሮ ቢጽ

አፍቅሮ ቢጽ ማለት፡- ወንድምን እንደ ራስ አድርጐ መውደድ ማለት ነው ።"እኔ እንደ ወደድኳችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ" ብሎ የፍቅርን ነገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሮአቸዋል።ዮሐ 13፥34።ቅዱስ ጳውሎስም "ወዘሰ አፍቀረ ቢጸ ኩሎ ሕገ ፈጸመ ገቢረ-ባልንጀራውን የሚወድ ሁሉ ሕግን ፈጽሞታል" በማለት ፍቅር የሕግ ፍጻሜ መሆኑን ተናግሮአል።ሮሜ 13፥8 እንደዚሁም፡- "በእነዚህም ሁሉ ላይ የሕግ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት"ይላል።

"የሕግ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅር ልበሱት" ይላል።ቆላ 3፥14

ወንድም (ባልንጀራ) የሚባለው በተፈጥሮ ሰው የሆነ የአዳም ልጅ ሁሉ ነው።ሰው ሁሉ በዘመን ብዛትና በትውልድ ሐረግ በመብዛቱ ባዕድ እየመሰለና እየተራራቀ ሄደ እንጂ በአኗኗሩና በባሕሉ ቢለያይም ከአንድ አባትና ከአንዲት እናት አዳምና ሔዋን የተገኘ ነው።

ፍቅር የሚገለጸውም እንዴት እንደሆነ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃልና በሥራ አሳይቶናል። "ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ቤዛ አድርጐ ከመስጠት የበለጠ ፍቅር ለማንም የለውም" ብሎ እንደ አስተማረ በቀራኒዮ አደባባይ በራሱ ፈቃድ ስለ እኛ በመስቀል የከበረ ደሙን አፍስሶልናል።ዮሐ 15፥13።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሕይወት ደኅንነትና ጥቅም ሲል የራሱን ሕይወት አሳልፎ እንደሰጠ ሁሉ እኛም ራሳችንን ለወንድማችን አሳልፈን እንድንሰጥ አርዓያውን ትቶልናል "እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን" በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ይመሰክራል።ፊል 2፥4።

ከዚህ የተነሣ ቅዱሳን የባልንጀራውን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስደሰት ብዙ ገድልና ትሩፋት ሠርተዋል ለምሳሌ ያህል የተወሰኑትን እንመልከት፡-

1.ሁለት አኃው ለተልዕኮ ወደ ከተማ በሄዱበት ጊዜ አንዱን በኃጢአት መውደቅ አጋጠመው በዚህ ጊዜ ጓደኛው ወደ ገዳማችን እንመለስ ቢለው እኔ በኃጢአት ስለወደቅሁ አልመለስም አለው።በኃጢአት የወደቀውን ጓደኛውን ለማበረታታት ብሎ እኔም እኮ በኃጢአት ወድቄአለሁ።ነገር ግን ወደ ገዳማችን ሂደን ቀኖና መቀበል አለብን በማለት ጓደኛውን አጽንቶ ወሰደውና ለጓደኛው ሲል ኃጢአት እንደፈጸመ አድርጎ አብረው ቀኖና ተቀብሎ እየሰገደና እየፈጸመ ላለው ስል እግዚአብሔር ይቅር ብያለሁ በማለት ቀኖናቸውን ሳይጨርሱ ድምፅ አሰምቷቸዋል።

2.አንድ አረጋዊ በአስቄጥስ ገዳም ታሞ በነበረበት ጊዜ ትኩስ ዳቦ ማን ባመጣልኝ እያለ ሲለምን ጓደኛው ሽፍቶች ያሉበትን በረሃ አቋርጦ ረጅም ርቀት ተጉዞ ብዙ ቀናት ፈጅቶ ከቀኑ ብዛት የተነሣም ትኩስነቱ ሳይለውጥ ዳቦውን አመጣለትና እንዲበላ ሰጠው መነኩሴው ግን ወንድሜ የራሱን ሕይወት በሞት ለውጦ ያመጣውን አልበላም ብሎ እምቢ ሲል እንዲበላ ለምነውት በልቶ ከሕመሙ ሊፈወስ ችሏል ይህም የዳዊትን ታሪክ ያስታውሰናል።1ዜና 11፥15-19።

3.ቅዱስ ጳኩሚስ አንዲት ሴት ብዙ አጋንንት ሠፍረውባት ስትሰቃይ ተመለከተና ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ የእርሷ ስቃይና በእርሷ የሠፈሩባት አጋንንት ወደ እርሱ እንዲዛወር በመጠየቁ ጌታ እንደ ጸሎቱ አደረገለት ሴትዮዋም ተፈውሳለች አባ ጳኩሚስ በብዙ ስግደትና ጾም ከጸሎት ጋር ከእርሱ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል።

እንዲያውም አጋንንቱ ተስፋ በመቁረጥ "በምን እናደርጋለን ከዚህ እንሂድ" ሲሉ "ለምን አትቆዩም ከወዳጃችሁ ቤት መጥታችኋልና ጥቂት ጊዜ አረፉ" እያለ ተሳልቆባቸዋል።ይህም የኤልያስን ታሪክ ያስታውሰናል።1ነገ 18፥25-29።

2.3.2.<u>ከአላዊያን ነገሥታት</u>

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት "ወእነግር ስምዓከ በቅድመ ነገሥት ወኢይትሐፈር-በነገሥታት ፊት ምስክርነትህን ቃልህን እናገራለሁ አላፍርምም።መዝ 118፥46 በማለት እንደተናገረው እንደ ሰው በእግዚአብሔር ከማያምኑ ነገሥታትና መኳንንት ጋር ታግለዋል

ጌታም በወንጌል ስለ እኔ ወደ ገዥዎችና ወደ ነገሥታት ትወሰዳላችሁ።ማቴ 10÷16 ብሏል ቅዱሳኑም ይህንን ተግባራዊ አድርገዋል።

- ኤልያስ ከአከዓብና ከኤልዛቤል፣ከልጃቸው አካዚያስ...ጋር
- ሠለስቱ ደቂቅ፣ዳንኤል ከናቡከደነጸር.....ጋር
- መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ከሔሮድስ.....ጋር
- ወንጌላዊው ዮሐንስ ከድምጥያኖስ ጋር .....መከራ ተቀብለዋል።

2.3.3.<u>ከመናፍቃን</u>

ጌታ በወንጌል የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂ ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች መምህራን ተጠንቀቁ።ማቴ 7÷51።በማለት እንዳስተማረው ቅዱሳን ከመናፍቃን የተቀበሉት መከራ ነገሥታት ካደረሱት መከራ አይተናነስም።

ሐዋርያው ጳውሎስም ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች በውስጣችሁ ይነሣሉ።ሐዋ 20÷28 እንዳለው በየዘመናቱ ቅዱሳኑን ያሳደዱ መናፍቃን እንደነበሩና በዘመናችንም እንዳሉ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳናል።

<u>ለምሳሌ</u>፡- አርዮሳውያን ሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስን

መላካውያን በወልድ ዋሕድ የሚያምኑ ዘጠኙ ቅዱሳንን

እነዚህን ለአብነት ያህል አነሣን እንጂ የቅዱሳን ተጋድሎ ብዙ ነው።መከራ የተቀበሉትም ከብዙ አካላት ነው።ዓይነቱም እጅግ በጣም ብዙ ነው።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል የነገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታችሁ ምሰሉአቸው በማለት የተናገረው ከቅዱሳን የተጋድሎ ዓይነት ሕይወት ተምረን አውደ ፍኖታቸውን እንድንከተል ነው።ዕብ 13÷7።

2.4. <u>ቅዱሳን መላእክት</u>

ቅዱሳን መላዕክት ተፈጥሮአቸው የተቀደሰ ሕይወታቸውም በቅድስና የተመላ በመሆኑ ቅዱሳን ይባላሉ።በመንፈሳዊ ዓለም እየኖሩ በሰማይም በምድርም እግዚአብሔርንና ሰውን ያገለግላሉ።በዚህ ተግባራቸው ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳን ሰዎች ጋር አንድነት አላቸው።

ከተፈጠሩበት ዕለትና ሰዓት ጀምሮ ከቅዳሴና ከማኅሌት ከአገልግሎት ተለይተው አያውቁም ዕረፍታቸው ምስጋናቸው፣ምስጋናቸውም ዕረፍታቸው ነው።ኢሳ 6፥3፣ራዕ 4፥8።

<u>፪.፩.የመላእክት ተፈጥሮና አሠፋፈራቸው</u>

ቅዱሳን መላእክት ተፈጥሮአቸው አይታወቅም ዳዊት በመዝሙሩ መላእክቱን መንፈስ (ነፋስ) አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ መዝ 103፥4።በማለት የተናገረው።

1.እንደ እሳትና ነፋስ ረቂቅ መሆናቸውን

2.ለተልዕኮ የሚፋጠኑ መሆናቸውን

3.ኃያልነታቸውን፣ፈጻምያነ ፈቃድ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው እንጂ ከእሳትና ከነፋስ ተፈጥረዋል ለማለት አይደለም።

ድርሳነ ሚካኤል ውስጥ "ሰላም ለገጽከ እምነፍስ ወነድ ዘተሥዕለ ምስለ ማይ ወመሬት ዘኢተሀወለ" የሚል ገጽ ንባብ ቢገኝም ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ከተናገረው ጋር ተመሳሳይ ነው እንጂ ተፈጥሮአቸው ከእሳትና ከነፋስ ማለት አይደለም።

መላእክት ከእሳትና ከነፋስ ተፈጥረዋል ከተባለ ኃላፋያን፣ጠፊዎችና መሬታውያን ናቸው ማለት ይሆናል።እሳትና ነፍስ ያልፋሉና "ሶበሰ ተፈጥሩ እምነፋስ ወእሳት እሞቱ ወእማሰኑ ከማነ ከእሳትና ከነፋስ ተፈጥረውስ ቢሆን ኖሮ እንደ እኛ በሞቱ" በማለት አክሲማሮስ ተናግሮአል።

የቅዱሳን መላእክት አሠፋፈርን በተመለከተ ቅዱስ ኤፍሬንዮስ አክሲማሮስ በተባለ መጽሐፉ እግዚአብሔር መላእክትን በዕለተ እሁድ ፈጥሮ በኢዮር፣በራማ፣በኤረር በከተማ አሥር በነገድ ደግሞ መቶ አድርጎ እንደሠፈራቸው ተናግሯል።

ቅዱሳን መላእክት በነገድ መቶ መሆናቸውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮአል።ማቴ 18፥12።ከመቶው አንዱ ዲያብሎስ ነበር በዲያብሎስ ፈንታም አዳም ተተክቷል "የጠፋውና የተፈለገው" አዳም ነው።

በከተማ አሥር ስለ መሆናቸውም ዐሥር ድራም ያላት ብትኖር አንዲቱ ብትጠፋባት መብራት አብርታ በቤቷ ያለውን ሁሉ እየፈነቀለች እስክታገኛት ድረስ ተግታ ትፈልግ የለምን በማለት አስረድቷል።ሉቃ 15፥8።

<u>በከተማ አሥር ማለት፡-</u>

1.<u>ኢዮር</u>፡- እግዚአብሔር በኢዮር ዐርባውን ነገደ መላእክት ለአራት ከፍሎ አራት አለቃዎችን ሹሞ አስፍሮአቸዋል።ኢዮርን እንደ ፎቅ ቤት አድርጐ በአራት ከተማ ከፍሏታል።

- በላይኛው ከተማ ዐሥሩን ነገድ አጋዕዝት ብሎ ሳጥናኤልን አለቃ አድርጐ ሾመላቸው ።
- በሁለተኛው ከተማ ዐሥሩን ነገድ ኪሩቤል ብሎ በመሰየም ኪሩብ የተባለውን መልአክ አለቃ አድርጐ ሾሞላቸዋል።ሕዝ10፥1።
- በሦስተኛው ከተማ ዐሥሩን ነገድ ሱራፌል ብሎ በመሰየም ሱራፊ የተባለውን መልዓክ አለቃ አድርጐ ሾመላቸው።
- በአራተኛው ከተማ ዐሥሩን ነገድ ኃይላት ብሎ በመሰየም ቅዱስ ሚካኤልን አለቃ አድርጐ ሾመላቸው።1ጴጥ 3፥22።እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሁኜ አሁን መጥቻለሁ።ኢያ 5፥14 ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጸናኝ የለም።ዳን 10፥21 ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል። ዳን 12፥10 የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ይሁዳ ቁ.9 እንዲል።

2.ራማ

እግዚአብሔር በራማ ሠላሳውን ነገደ መላእክት ከሦስት ከፍሎ ሦስት አለቃዎችን ሹሞላቸዋል።

- በመጀመሪያው ከተማ ዐሥሩን ነገድ አርባብ ብሎ በመሰየም ቅዱስ ገብርኤልን አለቃ አድርጐ ሾመላቸው።
- በሁለተኛው ከተማ ዐሥሩን ነገድ መናብርት ብሎ በመሰየም ቅዱስ ሩፋኤልን አለቃ አድርጐ ሾመላቸው።

- በሦስተኛው ከተማ ዐሥሩን ነገድ ሥልጣናት ብሎ በመሰየም ሱርያል የተባለውን መልዓክ አለቃ እድርጐ ሾለማቸው።1ጴጥ 3÷22።

3.ኤረር

እግዚአብሔር በኤረር መላእክትን ነገደ መላእክት ከሦስት ከፍሎ ሦስት አለቃ መድቦ ሹሞ አሰፈራቸው።

- በመጀመሪያ ከተማ ዐሥሩን ነገድ መመናብርት ብሎ በመሰየም ሰዳታኤል የተባለውን መልዓክ አለቃ አድርጐ ሾመላቸው።
- በሁለተኛው ከተማ ዐሥሩን ነገድ ሊቃናት ብሎ በመሰየም ሰላታኤል የተባለውን መልዓክ አለቃ አድርጐ ሾመላቸው።
- በሦስተኛው ከተማ ዐሥሩን ነገድ መላእክት ብሎ በመሰየም አናንኤል የተባለውን መልዓክ አለቃ አድርጐ ሾመላቸው።1ጴጥ 3÷22።

፪.፬.፪. <u>የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት</u>

ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ለአገልግሎት የሚፋጠኑ ናቸው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትና ቸርነት እውቀትና ጥበብ ይዘው ወደ ሰው ይመጣሉ።ዳን 9÷22።

የሰዎችን ጸሎትና ልመና ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ ሐዋ 9÷1።

እግዚአብሔርን በማመስገን የጸኑ ናቸው።ራዕ 4÷8 እኛንም፦

ሀ.<u>ያድኑናል</u>

የእግዚአብሔር መልዓክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሠፍራል ያድናቸውማል።መዝ 33÷7።

እስራኤልን ከፈርኦናውያን ማዳናቸው ዘጸ 14÷19።

ሠለስቱ ደቂቅንና ዳንኤልን ከእሳትና ከአንበሳ ዳን 3÷25፣ዳን 6÷22።

ቅዱስ ጴጥሮስን በእስር ቤት እንደጠበቀውና እንዳዳነው።ሐዋ 12÷11።

ለ.<u>ይራዱናል</u>

ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን ዕብ 1፥14።እንደተባለ

ነቢዩ ዳንኤልንም የእግዚአብሔር መልዓክ እንደ ዳሰሰው እንደ አበረታው።ዳን 10፥8-18።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በጌቴ ሴማኒ በሚጸልይበት ጊዜ የሚያበረታታው መልዓክ መታየቱ ሥጋ የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔር መልዓክ እርዳታ የሚያስፈልገው መሆኑን ያመለክታል።ሉቃ 22፥43።

ሐ.<u>የማልዱናል</u>

ሰባ ዘመን በባቢሎን እጅ በምርኮ ወድቀው በባርነት ለነበሩት እስራኤል የእግዚአብሔር መልዓክ ልመና ሲያቀርብ እግዚአብሔር መልካምና የሚያጽናና ቃል እንደመለሰለት።ዘካ 1፥12።

ሦስት ዓመት ተመላልሶ ፍሬ ያጣበት በለስ እንድትቆርጥ ጌታ ሲያዝዝ መልዓኩ እንደለመነ እንመለከታለን።ሉቃ13፥6።

መ.<u>ይዋጉልናል</u>

የምዕመናን ጦርነት ከሥጋውያንና ከደማውያን ጋር ሳይሆን ከአጋንንት ጋር መሆኑን መጻሕፍት በሙሉ ይናገራሉ።ኤፌ 6፥12።

አሦራውያን በሰናክሬም እየተመሩ ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት ሲመጡ የእግዚአብሔር መልዓክ ተዋግቶላቸዋል።ኢሳ 37፥36።

ሠ.<u>ይጠብቁናል</u>

- በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ ዘጸ 23፥20፣ዕብ 90፥6
- ክፉ ሰዎች (የሰዶምና የገሞራ) ሎጥን በከበቡት ጊዜ መላእክት ጠብቀውታል
- ነቢዩ ኤልሳዕ የነበረበትን የሰማሪያ ከተማና ሳምራውያንን ቅዱሳን መላእክትን ጠብቀዋል ስለ ነቢዩ ኤልሳዕ ቅድስና ፪ ነገ 6፥14።
- ቅዱሳን መላእክት የሰው ልጆችን እንደሚጠብቁ እነሆም አንድ ቅዱስ ጠባቂ ከሰማይ ወረደ በማለት ነቢዩ ዳንኤል ተናግሮአል።ዳን 4፥13።

ረ.ይካሰሱልናል

እያንዳንዱ ሰው በቀንና በሌሊት የሚጠብቁት ቅዱሳን መላእክት አለት መላእክት የእያንዳንዱን ሰው ሕይወት ከመጠበቅ ጋር ስለ ሚጠብቁት ሰው በእግዚአብሔር ፊት ይካሰሳሉ።

ሰይጣን ካህኑ ኢያሱን ለመክሰስ በእግዚአብሔር ፊት ሲቆም ተከራክሮ ያሳፈረው የእግዚአብሔር መልአክ ነው።ዘካ 3፥1።

ጌታም በወንጌል "ከእነዚህ ከትናንሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ።" ማቴ 18፥10። በማለት አስተምሮአል።

ሰ.በንሰሐችን ደስ ይላቸዋል፦

ሰው ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሞት ወደ ሕይወት በንሰሐ ሲመለስ በሰማይ ደስታ ያደርጋሉ።ሉቃ 15፥7።

፪.፫.፬. ባሕርያዊ ሥልጣናቸውና ክብራቸው

በተፈጥሮአቸው ረቂቅና ፈጣኖች የሆኑ ቅዱሳን መላእክት ባሕርያቸውን የሚገልጽ ሥልጣንና ክብር ተሰጥቷቸዋል።ለምሳሌ፦

ሀ.ኃያላን ናቸው

ቅዱሳን መላእክት የተሰጣቸው ኃይልና ሥልጣን ታላቅ ነው።ኃይላቸውና ሥልጣናቸው በሚገለጥበት ጊዜም ፍጥረት ሁሉ በፊታቸው ይንቀጠቀጣል።ዳን 10፥5-9፣ማቴ 28፥1-4።

ለ.ዓመፀኞችን ይቀጣሉ

- የሰዶምና የገሞራ ሰዎች ጻድቁን ሎጥን በአስጨነቁ ጊዜ ሁሉንም እውራን እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።ዘፍ 19፥1።
- የሰናክሬም ሠራዊትን ቀጥተዋል 2ነገ 19፥35

- በሐዋርያት የአገልግሎት ዘመን ሄሮድስ ለእግዚአብሔር ክብር ባለመስጠቱ በትል ተበልቶ እንዲሞት ተደርጓል።ሐዋ12፥21።

ሐ.<u>በፍርድ ቀን ተሳትፎ አላቸው</u>

- ወልደ እጓለ እምሕያው ክርስቶስ አስቀድሞ መላክቱን ይልካል ዓመጻ የሚያደርገውን ይለቅማሉ ወደ እቶነ እሳትም ይጥላሉ።ማቴ 13፥39።
- መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋልና ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከዐራቱ ነፍሳት ለእርሱ የተመረጠን ይሰባሰባሉ።ማቴ 24፥31።
- ጌታ ራሱ በትዕዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳልና።1ተሰ 4፥16።

መ.የጸጋ ጌትነት አላቸው

ጌትነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ አምላካችን እግዚአብሔር የኃይሉ መገለጫ የሆኑ ቅዱሳን መላእክትን በጸጋ ጌትነት አክብሯቸዋል።ይህንንም በሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጥ ይቻላል።

- ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድን ነው?ኢያ 5፥19
- ጌታዬ ሆይ ከራዕዩ የተነሣ ሕመሜ መጣብኝ ኃይልም አጣሁ ይህ የጌታዬ ባሪያ ከጌታዬ ጋር ይናገር ዘንድ እንዴት ይቻላል አልሁት።ዳን 10፥16።
- ጻድቁ ሎጥም መላእክት ሊያገለግሉት ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ ጌቶቼ ሆይ ወደ ባሪያችሁ ቤት አቅኑ እያለ ተማጽኗቸዋል።ዘፍ 19፥2።

ሠ.<u>ስግደት ይገባቸዋል</u>

ስግደት የባሕርይና የጸጋ ተብሎ በሁለት ይከፈላል

- ለቅዱሳን የሚቀርበው የጸጋ ስግደት ነው
- ለቅዱሳን መላእክት መስገድ የእግዚአብሔርን ጸጋ ማክበር ነው።ቅዱሳን ሰዎች ለቅዱሳን መላዕክት እንዲሰግዱ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል።

ኢያሱ 5፥14

ሎጥ ዘፍ 19፥1

ዳንኤል ዳን 10፥9

በዮሐንስ ራዕይ የተጻፈው ወንጌላዊው ዮሐንስ ለእግዚአብሔር መልዓክ በሰገደ ጊዜ መልዓኩ “እንደታደረገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር የኢየሱስ ስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ” ብሎታል።ይህንን በመያዝ ለመላእክት ስግደት አይገባም የሚሉ ሰዎች እንዳሉ ይታወቃል።

ቅዱስ ዮሐንስ የሰገደው ለቅዱሳን መላእክት ስግደት እንደሚገባ አውቆና ተረድቶ ነው። መልዓኩም አትስገድልኝ ያለው ትሕትናን ለመፈጸም ነው።ራዕ 19፥10።ዮሐንስ የእግዚአብሔር መልአክ አትስገድልኝ ካለው ከሰገደ በኋላም እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ሰግዷል መልዓኩም በተመሳሳይ ቃል አትስገድልኝ ብሎታል ራዕ 22፥9፣ምሳ 29፥23 እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል እንዲል።ያዕ 4፥6።

በሁለተኛም ደረጃ መልዓኩ አትስገድልኝ ያለው ለዮሐንስ የተሰጠውን ክብርና ቅድስና የነበረውን ንፅሕና ስለሚያውቅ ነው።

ምዕራፍ ሦስት

ክብረ ቅዱሳን

ልዑለ ባሕርይ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን የስሙ ቀዳሽ የክብሩ ወራሽ አድርጐ በአርአያውና በአምሳሉ በሕያውነት፣በነባቢነት፣በልባዊነት ግሩምና ድንቅ አድርጐ ፈጥሮታል።መዝ 138፥14።

ሰው የተፈጠረበትን ዓላማና ክብር በምክረ ከይሲ ተታሎ ቢያጣውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ወደ ቀደመ ክብሩ መልሶታል።በዚህም ሰውን ከሁሉም ፍጥረታት ይልቅ እንዳከበረውና እንደወደደው እንመለከታለን።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ቅዱሳን ክብር ሲናገር “ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ (ለቅዱሳን ሁሉ አብነት ይሆናቸው ዘንድ) አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቅድሞ ደግሞ ወስኗልና ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው”። ሮሜ 8፥29 ብሏል።

፫.፩. <u>የቅዱሳን ክብር መሠረት</u>

ለቅዱሳን የሚሰጠው ክብርና ጸጋ በተቀበሉት መከራ ልክ ነው። “ሁሉን ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት እቆጥረዋለሁ”በማለት የተናገረ ቅዱስ ጳውሎስ “በመከራችን ደግሞ እንመካለን” ማለቱ መከራ የክብር መገኛ መሠረት ስለሆነ ነው።ሮሜ 5፥5።ጊዜያዊ የሆነው መከራም የዘለዓለምን ክብር እንደሚያስገኝ ሲያስረዳም “ቀላል የሆነው ጊዜያዊው መከራችን የክብርን የዘለዓለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልኛልና” ብሏል።2ቆሮ 4፥17።

ቅዱስ ጴጥሮስም “በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ ስለ ክርስቶስ ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ። በማለት የሥጋ መከራ የክብር ምክንያት መሆኑን አስረድቷል 1ጴጥ 4፥13።

፫.፪. <u>ለቅዱሳን የተሰጠ ክብርና ሥልጣን</u>

ቅዱሳን እግዚአብሔርን በመከተላቸውና ስለ እርሱ የተለያዩ መከራዎችን መቀበላቸውና በትዕግስት ማሳለፋቸው እስከ ሞትም መጋደላቸውና መታመናቸው የተለያየ ጸጋና ክብር አሰጥቷቸዋል።

፫.፪.፩.<u>ስማቸው የከበረ ነው</u>

እግዚአብሔር አብርሃምን ስምህን አከብረዋለሁ ዘፍ 12፥7 በማለት ታላቅና ለበረከት የሆነ ሰው አድርጐታል።

የቅዱሳኑ ስም የከበረ በመሆኑ የእግዚብሔር ሰው ኤልያስ የሐሰተኞች ነቢያትና የጣኦት ሐሰተኛነት እንዲገለጥ መሥዋዕት ሠውቶ የተማጸነው በቅዱሳን ስም ነው።አቤቱ የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ ሆይ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደሆንክ እኔም ባሪያህ እንደሆንኩ ይህንንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ።በማለት 2ነገ 18፥32።

እግዚአብሔርም ወዳጁ ኤልያስ በቅዱሳኑ ስም ያቀረበውን ልመና ተቀብሎ ፈጽሞታል በመሆኑም በከበረ ስማቸው የሚጠሩት፦

- ቅዱሳት መካናት
- ዐጽማቸው ያረፈበት ቅዱስ ቦታ
- የለበሱት ልብስ ሐዋ 19፥11
- በስማቸው የሚፈልቁ ጠበላት ሐዋ5፥15
- አካላቸውና የአካላቸው ጥላ
- በስማቸው የተሣለ ሥዕላት ሁሉ ክብር አላቸው።

ምክንያቱም ቅዱሳን በረድኤት ከእነዚህ ሁሉ ጋር ይኖራሉና።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሥጋ ምንም እንኳ ብርቅ በመንፈስ ከእናንተ ነኝና ሥርዓታችሁንም በክርስቶስም ያለውን የእምነታችሁን ጽናት እያየሁ ደስ ይለኛል።ቈላ 2፥5 በማለት የተናገረው ከዚህ አኳያ ነው።

፫.፪.፪. <u>በእግዚአብሔር ገንዘብ ላይ የተሾሙ ናቸው</u>

የሚታየውና የማይታየው ዓለም ሁሉ የእግዚአብሔር ገንዘብ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ።መዝ 23፥1፣መዝ 49፥9-12።

የፍጥረት ሁሉ ባለቤት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ቅዱሳኑን በሥነ ፍጥረት ሁሉ ላይ እንደሾማቸው "እንኪያስ ምግባቸውን በየጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ በቤተሰቦች ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማነው?ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው። እውነት እውነት እላችኋለሁ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል።ማቴ 24፥45። በማለት አስተምሮአል።

ቅዱሳንም ፈጣሪያቸው ጽድቅ ለሰሩበትና እርሱን ሊያገለግሉት የሰጣቸውን አካልና አዕምሮ እንዲሁም ጊዜ በንፅሕና እና በቅድስና ጠብቀው በሞት እስኪጐበኛቸው ድረስ ተድላ ሥጋ ከማድረግ ተቆጥበው ራሳቸውን ለጌታቸው ለክርስቶስ ያስረከቡ ናቸው።በመሆኑም በእጁ ሥራ ሁሉ ላይ፣በሥነ ፍጥረት ሁሉ አሰልጥኖአቸዋል ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን እንመልከት፦

ሀ.በሰማይና በምድር ላይ

ሰማይና ምድር የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ናቸው።የሚያዝዛቸውም እግዚአብሔር ነው።ነገር ግን ለአምልኮቱ ቀናእያን የሆኑ ቅዱሳን በሰማይና በምድር ሥልጣን ተቀብለዋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ይሀንን ሲያስረዳ ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም ሁለተኛም ጸለየ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ።ያዕ 5÷17። ሰማይና ምድርን ማዘዝ ዝናማትን ማዝነምና መከልከል የሚችል የፈጠራቸው እግዚአብሔር ብቻ ሲሆን ይህን ግን ኤልያስ ሲያደርግ ተመልክተናል።

ለ.በፀሐይና በጨረቃ

ፀሐይና ጨረቃ ለሰው ብርሃን በመስጠትና በጊዜ መለኪያነት እንዲያገለግሉ በትዕዛዘ እግዚአብሔር የተፈጠሩ ናቸው።ዘፍ 1÷16 ነገር ግን ፀሐይና ጨረቃን ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ ቅዱሳን ሰዎች ሲያዝዟቸው እናገኛለን።የእግዚአብሔር ሰው ኢያሱ ከአሕዛብ ጋር ሲዋጋ፡-

“በገባዖን ላይ ፀሐይ ትቁም፣በኤሎንም ሸለቆ ጨረቃ፣ሕዝቡም ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ ፀሐይ ቆመ፣ጨረቃም ዘገየ፣አንድ ቀንም ያክል ለመግባት አልቸኮለም”።ኢያ 10÷12። በማለት ማዘዝ ችሏል።

ከኢያሱ በኋላም ኢትዮጲያውያኑ ቅዱሳን አቡነ አሮን ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ አባ ዜና ማርቆስ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል በሚለው አምላካዊ ቃል በመታመን የተፈጥሮ ሥርዓታቸውን ጠብቀው በጠፈር ላይ የሚጓዙትን ፀሐይና ጨረቃ ማዘዝ ችለዋል።

ሐ.በርኩሳን መናፍስት ላይ

ርኩሳት መናፍስት ሰውን በመቆራኘት የተለያዩ የአካልና የስነ ልቦና ጉዳት በማድረስ የሚጐዱ ናቸው።

- መምህር ሆይ ዲዳ መንፈስ ያደረበትን ወደ አንተ አምጥቸዋለሁ በያዘውም ሥፍራ ሁሉ ይጥለዋል አረፋም ይደፍቃል።ማር 9፥17።
- እነሆም ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት ነበረች እርስዋም ጎባጣ ነበረች ቀንታም ልትቆም ከቶ አልታቻላትም።ሉቃ 13፥11።
- እነዚህናም ሌሎችንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ፈውሷቸዋል።

አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲያወጧቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ሥልጣንን ሰጣቸው።ማቴ 10፥1።ይላል ይህን ሥልጣን እንጀራ ለመብላትና መልኩን ለማየት ለተከተለው ሕዝብ ሁሉ አይደለም በዚህም ሥልጣን፦

- አጋንንትን በስሙ ገዝተዋል።ሉቃ 10፥17።
- ርኩስ መንፈስን በስሙ በመግሠጽ አስወጥተዋል።ሐዋ 16፥16።

መ.<u>በሞት ላይ</u>

- የሞት መሠረታዊ ትርጉም የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው
- ከእግዚአብሔር ፈቃድ ርቃ የምትኖር ነፍስም በእግዚአብሔር ዘንድ የሞተች ናት ይህቺም ነፍስ በሕይወት ጸንታ ካልኖረች በመጨረሻው ዘመን ለሰይጣንና ለመልዕክተኞቹ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት መሄድ እድል ፈንታዋ ይሆናል።ማቴ 25፥41።

ነገር ግን የሞት ሥልጣን በክርስቶስ ተሽሯል

የዕለት ሬሳ ወለተ ኢያኢሮስን።ማር 5፥22-43።ወልደ መበለትን ሉቃ 7፥11።

የአራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን።ዮሐ 11፥43። በራሱ ሥልጣን ከሞት አስነስቷል።

ቅዱሳን ሐዋርያትም አምላካችን በሰጣቸው ሥልጣን ሙታንን አስነስተዋል ለምሳሌ፦

- በኢዮጴ ነዋሪ የነበረችን ጣቢታን ቅዱስ ጴጥሮስ።ሐዋ 9፥36
- በጢሮአዳ ከተማ ጳውሎስ በሌሊት ሲያስተምር ከፎቅ ላይ ወድቆ የሞተው አውጢኪስን ቅዱስ ጳውሎስ።ሐዋ 20፥9-12።በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አስነስተዋል።

- ቅዱስ መቃርስ ብዙ ተከታይ የነበረው አንድ መናፍቅ ከሙታን መካከል አንዱን አስነስተህ ካላሳየኸኝ ትንሣኤ ሙታን መኖሩን አላምንም ባለው ጊዜ መናፍቁንና የሚከተለውን ሕዝብ በመያዝ ወደ መቃብር በመውሰድ በዚህ ሰው ክህደት ይህ ሕዝብ እንዳይጠፋ እለምንሃለሁ ብሎ ጸሎት ሲያደርግ ከሞተ ብዙ ዘመን የሆነው አንድ አስክሬን ተነሣ።ቅዱስ መቃርስም የተነሣውን ሰው በሕዝብ ሁሉ ፊት ጠየቀው ሰውየውም ያላመነና ያልተጠመቀ እንደሆነና በሲኦል በመከራ ይኖር እንደነበር ተናግሮ "አሁን ግን ፈጣሪዬ ሂድ ወዳጄ መቃርዮስ ይጠራሃል ብሎኝ መጣሁ" በማለት ሲመሰክር መናፍቅና ተከታዩ ሕዝብ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊያምን ችሏል።

ይኸው ቅዱስ መቃርስ በሌላ ጊዜ አንዲት ሴት ስታለቅስ አያትና ምን እንደሚያስለቅሳት ጠየቃት እርሷም ባሏ የሰው ገንዘብ በአደራ አስቀምጦ የት እንዳደረገው ሳይነግራት በድንገት በመሞቱ የገንዘቡ ባለቤት እርሷንና ልጆቿን ባሪያ ሊያደርጋቸው በመሆኑ እንደምታለቅስ ነገረችው።በዚህ ጊዜ ቅዱስ መቃርስ ከዚያ ሰው መቃብር ሂድ በስሙ ጠርቶ ገንዘቡን የት እንዳስቀመጠው ጠየቀው ሰውየውም ቦታውን ተናገረ፣ቅዱሱም ለሴትየዋ ቦታውን ነገራትና ገንዘቡ ተገኘ ገንዘቡን ለባለቤቱ በመስጠትም ከባርነት ልትድን ችላለች።

፫.፫. <u>እግዚአብሔርን ምሥጢሩን የሚገልጽላቸው ናቸው።</u>

አንድ ሰው በልቡ ውስጥ ያለውን ምሥጢር የሚያጫውተው ለልብ ወዳጁ ነው። እግዚአብሔርም ምሥጢሩ ሊያደርገው የወደደውን የሚገልጸው ለወዳጆቹ ቅዱሳን ነው።

1.የሰዶምና የገሞራ ጥፋት አስቀድሞ ለአብርሃም መገለጡ እግዚአብሔርም አለ "እኔ የማደረገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን" በማለት ገልጦታል።ዘፍ 18፥18።

2.የሰብአ ትካትን በማይ አይህ መጥፋት ለኖኅ በመናገር ወዳጄ ኖኅ መርከብ ሠርቶ ከጥፋት ውኃ እንዲድን ማድረግ ብቻም ሳይሆን በመርከብ ሥራ መላእክት እንዲያግዙት አድርጓል።

ይህንንም በዘፍ 6፥13 መመልከት እንችላለን

3.ለአዳም የገባውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ሰው እንደሚሆኑና ከድንግል ማርያም እንደሚወለዱ ለነቢያት ገልጸላቸዋል።ኢሳ 7፥14።ተረፈ ኤር 11፥52።

4.ዓለምን ለማሳለፍ ዳግም እንደሚመጣ በመጀመሪያ ለነቢያት በኋላም ለቅዱሳን ሐዋርያት ገልጠላቸዋል መዝ 49፥1፣ዘካ 14፥4፣ማቴ 24፥1።

እግዚአብሔር ምሥጢሩን ከቅዱሳኑ እንደማይሰውር ነቢዩ አሞጽ ሲያስረዳ፡-በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በስተቀር ምንም አያደርግም አሞ 3፥7 በማለት ነው።

ባለቤቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቷችኋል ብሏቸዋል።ማቴ 13፥16።

፫.፬.<u>የዓለም ብርሃን ናቸው</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ብሎ ስለ ራሱ የባሕርይ ብርሃንነት ከተናገረ በኋላ "የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል።እንጂ በጨለማ አይመላለስም" ዮሐ 8፥12።በማለት በተናገረው አምላካዊ ቃሉ መሠረት ቅዱሳን ያላቸውን ሁሉ ትተው የተከተሉት ስለሆነ የብርሃን ልጆች ከመሆን አልፈው "እናንት የዓለም ብርሃን ናችሁ"።የሚለው ተፈጽሞላቸዋል።ማቴ 5፥14።

፫.፭.<u>አማልክት ዘበጸጋ ናቸው</u>

አምላክነትና ቅድስና ብርሃንነትና ሌሎችም ሁሉ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ናቸው። ፊጥro የሚገዛ የሚመግብና የሚጠብቅ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ማንም የለምና።እናም እግዚአብሔር በአምላክነቱ የሚመስለውና የሚተካከለው ማንም የለም በማን ትመስሉኛላችሁ? ከማንስ ጋር ታስተካክሉኛላችሁ? እንመሳሰል ዘንድ ከማን ጋር ታስተያዩኛላችሁ?።ኢሳ 46፥5። እንዲል።ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም "አልቦ አምላክ ዘእንበለ እግዚአብሔር ወአልቦ እግዚአብሔር ዘእንበለ አምላክነ ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ የለም ከአምላካችንም በቀር እግዚአብሔር የለም ይላል"።መዝ 17፥31።

አምላክነት የእግዚብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ሲሆን ከቸርነቱ ብዛትና ከቅዱሳን ተጋድሎ የተነሣ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ አማልክት ዘበጸጋ እንዲሆኑ አድርጓል።

- ሙሴን ወደ ፈርኦን ሲልከው አምላክ አድርጎ ነው።ዘጸ 7፥1።
- ክቡር ዳዊትም አንሰ እቤ አማልክት አንትሙ ወደቂቀ ልዑል ኩልክሙ እኔ አማልክት ናቸው።ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ አልሁ ይላል።መዝ 81፥6።

ጌታችንም በወንጌል የዳዊትን "ቃል በመጥቀስ የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን እነዚያን አማልክት ካላችው የመጽሐፍ ቃል ሊሻር አይችልም"።በማለት የቅዱሳንን የጸጋ አምላክነት አረጋግጦታል።ዮሐ 10፥34።

፫.፮. <u>የቅዱሳን የክብር መገለጫ</u>

ቅዱሳን በእግዚአብሔር ገንዘብ የተሾሙ እውነተኛ የእግዚአብሔር አካላት የእግዚአብሔር የምሥጢር ሰዎች የብርሃን ልጆችና ራሳቸውም ብርሃንና አማልክት ዘበጸጋ መሆናቸውን ተመልክተናል ቅዱሳን የእነዚህ ክብር ባለቤቶች በመሆናቸው አምላካቸውና አባታቸው እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ ለክብራቸው መገለጫ እንዲሆን የሰጠውን እንመለከታለን።

3.6.1. <u>በስማቸው ቤተ ክርስቲያን ማነጽ መሥራት</u>

እግዚአብሔር፦ሰንበቴን ስለሚጠብቁ፣ደስ የሚያሰኝ ነገር ስለሚመርጡ፣ቃል ኪዳኔን ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና።በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣችኋለሁ።የማይጠፋ የዘላለም ስም እሰጣችኋለሁ።ያገለግሉት ዘንድ የእግዚአብሔርንም ስም ይወድዱ ዘንድ ባሪያዎቹ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር የሚጠጉት መጻተኞች እንዳያረክሱት ሰንበትን የሚጠብቁትን ቃል ኪዳኔንም የማይዙትን ሁሉ ወደ ተቀደሰ ተራራዬ አወጣቸዋለሁ።በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ።ኢሳ 56፥3።ሲል በስማቸው ቤት እንደሚሠራላቸው አዝዟል።

እነዚህም በማቴ 19፥10 ላይ በሦስት ደረጃ የተጠቀሱት ጃንደረቦች ናቸው።

3.6.2. <u>በስማቸው የተቀደሱ ነገሮችን መሰየም</u>

እግዚአብሔር ለቅዱሳን በስማቸው ቤተ ክርስቲያን እንደሚሠራ ብቻም ሳይሆን

- ጽላት እንዲቀረጽ
- ጸበል እንዲፈልቅላቸው
- ሰዎች በስማቸው እንዲጠሩላቸው አድርጓል “በቤቴና በቅጥሬ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ ያለው ከዚህ አኳያ ነው።

3.6.3. <u>የጸጋ ስግደት መስገድ</u>

ስግደት የአክብሮት፣የተገገርነት እንዲሁም የትህትና መገለጫ ነው።ዓላማው የሚወሰነውም እንደሚሰገድለት አካል ማንነት ነው።ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ስግደት የአምልኮ መገለጫ ሲሆን፤ለቅዱሳኑ ደግሞ የአክብሮት መገለጫ ነው።በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ስግደት ለቅዱሳን እንዲገባ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል።

- *አብድዩ በኤልያስ ፊት መስገድ 1ነገ 18÷7*
- *ናቡከደነጾር ለዳንኤል መስገዱ ዳን 2÷46*
- *የወኅኒ ቤት ጠባቂው ለቅዱስ ጳውሎስና ለሲላስ መስገዱ ሐዋ 16÷25*
- *የመቶ አለቃው ቆርኔሌዎስ ለቅዱስ ጳውሎስ መስገዱ ሐዋ 10÷25*

ምዕራፍ አራት

የቅዱሳን ምልጃ

በግዕዝ ቋንቋ “ተንበለ” ብሎ ለመነ፣አማለደ ይላል።አማላጅ ማለት አንዱ ስለሌላው የሚያደርገው ጸሎትና ልመና ነው።የሚለመነው እግዚአብሔር ሲሆን የሚያማልዱት ደግሞ ቅዱሳን ናቸው።በአማላጅነት ተግባር ውስጥ ሦስት አካላት መካተት ይኖርባቸዋል።

4.1.<u>አማላጅ</u>፦-ማማለድ የፍጡራን የቅዱሳን ሰዎች ተግባር ነው።የሚማልዱትም ስለ ኃጥአን ሰዎች ነው።የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ወደ እግዚአብሔር “ወዮ እነዚህ ሕዝቦች ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል።ለራሳቸውም የወርቅ አማልክት አድርገዋል።አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ያለበለዚያ ግን ከጻፍከው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ” በማለት መሥዋዕትነት እስከ መከፈል ድረስ ለመነ።ዘጸ 32፥31።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም “ብዙ ኃዘን የማያቋርጥም ጭንቀት አለብኝ ስል በክርስቶስ ሁኜ እውነትን እናገራለሁ አልዋሸም ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል።በሥጋ ዘመዶቼ ስለሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና” ብሏል።ሮሜ 9፥1።

ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኙ የእግዚአብሔር ባለሟሎች ናቸው።ጸሎታቸው ፈጥኖ ይሰማል።ልመናቸው ተቀባይነት አለው ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴና ካህኑ ሳሙኤል ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊትና ቃል በቃል የመነጋገር ክብር ነበራቸው።ዘኁ 12፥7፣1ሳሙ 2፥26።

4.2.<u>ተማላጅ</u>፦- ተማላጅ ማለት ምልጃ ጸሎትና ልመና ተቀባይ ማለት ነው።በሃይማኖት ትምህርት የጸሎት ሁሉ መድረሻ እግዚአብሔር ነው።ምልጃ ጸሎት እና ልመና የሚቀርብለት እግዚአብሔር አንድ ነው።አንድ እግዚአብሔር ስንል አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ማለታችን ነው።ሦስት አካል በአንድ ጌትነት በአንድ ሥልጣን በአንድ ፈቃድ

በአንድ መለኮታዊ ክብር የተስማሙ ናቸው።በሰማይና በምድር የሚገኙ የፍጥረታትን ልመና ተቀብለው የፈቃዳቸውንና የቸርነት ሥራቸውን ይሠራሉ።

4.3. **<u>የሚማለድለት</u>**፡- አማላጆች በአንድንትና በሦስትነት ወደ ሚመሰገን እግዚአብሔር ምልጃ የሚያቀርቡለት ስለ ኃጥአን ሰዎች ነው። የሚጸልዩለት ወይም የሚማልድለት ሕዝብ በአማላጅነት ሥራ ውስጥ የራሱ ድርሻ አለው በአማላጅ ጸሎትና በተማላጅ ቸርነት አምኖ ከሚሠራው ኃጢአት በንሰሐ መመለስ አለበት።

ለዚህ ማስረጃ የሚሆነን በባቢሎን ምርኮ የነበሩ እስራኤል ዘሥጋ ነቢዩ ኤርምያስን "አምላክህ እግዚአብሔር በአንተ እጅ ወደ እኛ የላከውን ነገር ሁሉ ባናደርግ እግዚአብሔር በመካከላችን እውነተኛና ታማኝ ምስክር ይሁን የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ቃል በመስማታችን መልካም እንዲሆንልን መልካም ወይም ክፉ ቢሆን አንተን ወደ እርሱ የምንልከውን የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ቃል እንሰማለን" ነበር ያሉት።ኤር 42፥5።

የሚማለድለት ሰው ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ካልሆነ በቅዱሳኑ ጸሎትም ካላመነና የሚለመንለት ሰው ሁኖ ካልተገኘ ቅዱሳን ጸሎታቸውን እንዲያቆሙ እግዚአብሔር ይነግራቸዋል።

- በእስራኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሀት ለሳኦል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው 1ሳሙ 16፥1።
- እንግዲህ አልሰማህምና ስለዚህ ሕዝብ አትጸልይ ስለ እነርሱም ልመናና ጸሎት አታድርግ አትማልድላቸው።ኤር 7፥16።
- ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙም ልቤ ወደ ዚህ ሕዝብ አያዘነብልም ከፊቴ ጣላቸው ይውጡ ኤር 15፥1።በማለት ካህኑ ሳሙኤልንና ነቢዩ ኤርሚያስን አናግሮአቸዋል።

4.4. <u>ምልጃ የእግዚአብሔር ትዕዛዝና ፈቃድ መሆኑ</u>

ምልጃ በሰው ፈቃድ የተደረገና የተጀመረ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ሰዎች እንዲፈጽሙት ያዘዘውና የፈቀደው በጐ ነገር ነው።ይህንንም በሚከተለው ጥቅሶች መረዳት እንችላለን።

የጌራራ ንጉሥ አቤሜሌክ የአብርሃምን ሚስት ሣራን በወሰደ ጊዜ እንዲመለስ ካስጠነቀቀው በኋላ ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልያል።አንተም ትድናለህ በማለት ራሱ እግዚአብሔር አቤሜሌክን እንዳዘዘው እናስተውላለን።ዘፍ 20፥1-7።

- ኢዮብን በነገር ሲያቆስሉት የነበሩትና በመጨረሻም ሊጠይቁት የመጡት ሦስቱ ወዳጆቹን እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስላላደረጋችሁ (ስለ እኔ አልተናገራችሁምና) ቁጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዶአል።አሁንም ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ሂዱ ባሪያዬ ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል።እኔም እንደ ስንፍናችው እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ ብሏል።ኢዮብ 42፥7።
- ቅዱስ ጳውሎስም የአማላጅነት ሥራ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የቅዱሳን ሥራ መሆኑን ሲገልጽ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንዲማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናችኋለን።ብሏል 2ቆሮ 5፥19። ለደቀ መዝሙር ጢሞቴዎስም በላከለት ክታቡ የአማላጅነት ሥራ ከሁሉም በፊት መደረግ እንዳለበት ሲገልጽ …..ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለነገስታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራችኋለሁ።ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው። በማለት የአማላጅነት ሥራ የእግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዝ እንጂ የሰው አሳብ አለመሆኑን መስክሮአል።1ጢሞ 2፥1-4።

4.5.<u>የአማላጆች አስፈላጊነት</u>

አማላጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውን ቀደም ብለን ተመልክተናል።አማላጆች የሚያስፈልጉበት ዋናው ምክንያት፦

- የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻደቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው በመሆኑ መዝ 33፥15።
- የኃጥአን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ የቅኖች ጸሎት ግን በእርሱ ዘንድ የተወደደ በመሆኑ ምሳ 15፥8።
- እግዚአብሔር ከኃጥአን ስለሚርቅ የጻድቃንን ጸሎት ግን ስለሚሰማ።ምሳ 10፥29።

- በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል ስለተባለ።ዮሐ 15፥7።
- የቅዱሳን ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ስለምታደርግ።ያዕ 5፥16።
- የቅዱሳን ጸሎት በመልዓኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ስለ ወጣ።ራዕ 8፥3-5።
- የቅዱሳን ናፍቆት ስለ እኛ በመማለድ ከእግዚአብሔር የማሰልጠን ጸጋና በረከት ማየት ስለሆነ 2ቆሮ 9፥13።
- የቅዱሳን ጸሎት በሽተኛውን ስለሚያድን ኃጢአትንም ስለሚያስተሰርይ።ያዕ 5፥14።

4.6.<u>የቅዱሳን አማላጅነት በዐፀደ ሥጋ</u>

ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ ሳሉ እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሲል ምሕረትንና ይቅርታን እንደ ሚያደርግ በነቢዩ አድሮ እንዲህ ይላል "ወይን በዘለላው በተገኘ ጊዜ በረከት በእርስዋ ላይ አለና አታጥፉት እንደሚባለው ሁሉን እንዳላጠፋ ስለ ባሪያዎቼ እንዲሁ አደርጋለሁ"።ኢሳ 65፥8።

እግዚአብሔር ስለ ወዳጆቹ ሲል ምሕረትን እንደሚያደርግ ምሳሌውን ከነትርጉሙ አስረድቷል።ከወይን ዛፍ ዘለላ ፍሬ በተገኘ ጊዜ ሊቆረጥ የነበረው ዛፍ ስለ ፍሬው ሲባል ይቆይ ተብሎ ከጥፋት እንደሚድን ሁሉ ቅዱሳን ያሉበትን ሕዝብና ሀገርም እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሲል ከማጥፋት ይታገሣል።ለምሳሌ የሚከተሉትን መመልከት እንችላለን።

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ስለ ሰዶምና ገሞራ ጥፋት በነገረው ጊዜ ይምራቸው ዘንድ ደጋግሞ ለምኗል ነገር ግን በሰዶምና በገሞራ አምሳጻድቃን ቀርቶ አምስት ጻድቃን እንኳን ባለመገኘታቸው በእሳት ልትቃጠል በቅታለች።ዘፍ 18፥22-ፍጻሜ።
- ሙሴ ከደብረ ሲና አሠርቱ ቃላት የተጻፈባትን ጽላት ይዞ ሲወርድ እስራኤላውያን ደግሞ አምልኮ ጣዖት ጀምረው ስለነበር እግዚአብሔር ተቆጥቶ ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ።በማለት ሙሴን ሲያናግረው ሙሴ ግን ከመዓትህ ተመለስ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ እያለ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር በመጸለዩ ተቆጥቶ ሊያጠፋቸው የነበረ እግዚአብሔር

የሙሴን ምልጃ ተቀብሎ እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ ይለናል።ዘጸ 32፥10-14።

ይህንንም ሙሴ ሲገልጸው፦ ስለ ሠራችሁት ኃጢአት ሁሉ እርሱንም ለማስቆጣት በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር ስለ አደረጋችሁ እግዚአብሔር ሊያጠፋችሁ ከተቆጣችሁ ከቁጣውና ከመዓቱ የተነሣ ስለፈራሁ እንደ ፊተኛው በእግዚአብሔር ፊት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ወደቅሁ እንጀራም አልበላሁም ውኃም አልጠጣሁም እግዚአብሔርም በዚያን ጊዜ ደግሞ ሰማኝ።ዘዳ 9፥18።ብሏል

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ይህንን ታሪክ ሲገልጸው እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅስፈት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኑሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ በማለት ነው።

በፊቱ ባይቆም ኑሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናግሯል ማለቱ ሙሴ በአማላጅነት ባይኖር ኑሮ እግዚአብሔር ያጠፋቸው እንደነበር ሲገልጽ ነው።መዝ 105፥23።

- ኢዮርብዓም የተባለ የእስራኤል ንጉሥ ጣያት በማምለኩ ይገሥጸውና ይመክረው ዘንድ የተላከውን ነቢይ በትዕቢት ለመያዝ የዘረጋው እጅ ስለ ደረቀ ደንግጦ ያንኑ የእግዚአብሔር ነቢይ አሁን የአምላክህን የእግዚአብሐርን ፊት ለምን እጂም ወደ እኔ ትመለስ ዘንድ ስለ እኔ ጸልይ አለው ያም ነቢይ እግዚአብሔርን ለመነ የንጉሡም እጅ ወደ እርሱ ተመልሳለች እንደ ቀድሞም ሆነች።2ነገ 13፥1-10።
- እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ብዛት መከራ በከበባቸው ጊዜ በአንድነት ወደ ኤርሚያስ ቀርበው "ዓይኖችህ እንዳዩን ከብዙ ጥቂት ቀርቶናልና ልመናችን እባክህ በፊትህ ትድረስ አምላክህም እግዚአብሔር የምንሄድበትን መንገድና የምናደርገውን ነገር ያሳየን ዘንድ ስለ እኛ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ አሉት።ነቢዩ ኤርሚያስም እኔ እንደ ቃላችሁ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ አላቸው።እግዚአብሔርም ኤርሚያስ የጸለየውን ጸሎት ሰምቶ በእርሱ አማካኝነት ለሕዝቡ የሚያጽናና የምሕረት መልእክት እንዲህ በማለት ላከ ስላደረግሁባችሁ ክፉ ነገር ተጸጽቻለሁና በዚህች ምድር ብትቀመጡ እሠራችኋለሁ እንጂ አላፈርሳችሁም፣እተክላችኋለሁ እንጂ አልነቅላችሁም፣ከምትፈሩት ከባቢሎን ንጉሥ

አትፍሩ አጸናችሁም ዘንድ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝና አትፍሩ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኤር 42÷2፣9÷11።

- በመጽሐፍ ቅዱስ ይህን የመሰለ በርካታ ነገር እናገኛለን ነገር ግን ለጠቢብ አንድ ቃል ይበቃዋልና አማላጅነት ለቅዱሳን የተሰጠ መሆኑን ለመረዳት የቀረቡት ማስረጃዎች ከበቂ በላይ ናቸው።

4.7.<u>የቅዱሳን አማጅነት በጸፀደ ነፍስ</u>

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሞት እጅግ በጣም ያስፈራና ይፈራ ነበር።ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ሁኔታ ሲገልጽ "በሕይወታቸው ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ ብሏል"።ዕብ 2÷14-16።ሞት ከክርስቶስ ትንሣኤ ወዲህ አስፈሪነቱ ቀርቷል።እንዲያውም ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ ሲያል ሆይ ድል መንሳትህ የት አለ እያሉ ሲንቁትና ሲዛበቱበት እንመለከታለን።1ቆሮ 15÷55።

ቅዱሳን በዚህ ዓለም የተሰጣቸው የማማለድ ጸጋና ሥልጣን ከዕረፍታቸው በኋላም በጸፀደ ነፍስ አይነሳቸውም በሚከተሉት ጥቅሶች እናረጋግጣለን።

1.ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ለክርስቲያኖች ከወጣኒነት ጀምሮ እስከ ፍጹምነት ድረስ በእግዚአብሔር ዘንድ ተዘጋጅቶ ያለውን ክብር ዘርዝሮ ካስረዳ በኋላ፦

ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ምንም ብታውቁ በእናንተ ዘንድ ባለ እውነት ምንም ብትጸኑ ስለ እነዚህ ዘወትር እንዳሳስባችሁ ቸል አልልም ሁልጊዜም በዚህ ማደሪያዬ ሳለሁ በማሳሰቤ ላነቃችሁ የሚገባኝ ይመስለኛል።ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመለከተ ከዚህ ማደሪያዬ መለየቴ ፈጥኖ እንዲሆን አውቃለሁና ከመውጣቴም በኋላ እነዚህን ነገሮች እንድታስቡ በየጊዜው ትችሉ ዘንድ እተጋለሁ 2 ጴጥ1÷13-15። በማለት ከሞት ከተለየ በኋላም እንደሚለምንላቸው ነግሮናል።

ቅዱሳን ከዕረፍታቸው በኋላ በዚህ ዓለም ያደርጉት እንደነበረው በጸምና በጸሎት በስግደት ልዩ ልዩ መከራ መቀበል ባይኖርባቸውም በዚህ ዓለም ሳሉ የሠሩትን ትሩፋትና የተቀበሉትን ቃል ኪዳን እያሳሰቡ በጸሎታቸው የሚታመኑትንና ስማቸውን የሚጠሩትን ሰዎች ሲራዱበትና ለክብር ሲያበቁበት ይኖራሉ።ይህም የሚደረግላቸው አስቀድሞ በዚህ

ምድር ሳሉ በሠሩት ሥራ መሆኑ በዮሐንስ ራዕይ ሥራቸው ይከተላቸዋል።ተብሎ ተገልጸአል።ራዕ14፥13።

2.ታሪኩና ሐተታው በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 16፥19-ፍጻሜ እንደተገለጸው አብርሃም በአካለ ነፍስ ሁኖ እንደተለመነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ሆኖ ተናግሮአል።

3.በመጽሐፈ ሄኖክ 9፥22 ላይ ከዚያም ቦታ ዓይኖቼ ከመላእክት ጋር የሚኖሩበት ማደሪያቸው ከቅዱሳንም ጋር የሚኖሩበት ቦታዎችን አየሁ ስለ ሰው ልጆችም ፈጽመው ይለምናሉ፣ይጸልያሉ፣ በማለት ቅዱሳን በዚህ ዓለም ስለሚኖሩ ሰዎች እንደሚለምኑ ተገልጿል።

እንዲሁም በምዕራፍ 12፥34 ላይ “በሰማይ የማኖሩ ጻድቃን በአንድ ቃል ሁነው ተባብረው ያመሰግናሉ፣ለሰውም ፈጽመው ይለምናሉ” ሲል በዐፀደ ነፍስ ያሉ ጻድቃን በዚህ ምድር ላሉ ሰዎ እንደሚጸልዩ ተናግሮአል።

<u>መወወያ ጥያቄ፡-</u> ያልሞተ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻል የሚለውን ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ አያማልዱም ለማለት መናፍቃን ይጠቀሙበታልና እንዴት ይታያል መክ 9፥4?

ምዕራፍ አምስት

ማዕረጋተ ቅዱሳን

መንፈሳዊ ሕይወት የቅድስና ኑሮ እንደ መሆኑ መጠን ከአብራክ መንፈስ ቅዱስና ከማኅፀነ ዮርዳኖስ በጥምቀት ዳግም በመወለዱ የሚጀምርና ደረጃውን የጠበቀ ዕድገት ያለበት ሕይወት ነው።ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንከል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ እንዲል 1ጴጥ 2÷3።

ቅዱሳንም ከወጣንያን ጀምረው በጸጋ እግዚአብሔር እየተጐበኙ ወደ ፍጹምነት ይደርሳሉ። ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል፣ያጸናችሁማል፣ ያበረታችሁማል።እንዲል።1ጴጥ 5÷1-11።

በወጣኒነት ጀምረው ፈተናውን እያሸነፉ ሲሄዱ በማዕከላዊነት ደረጃ አድርገው በመጨረሻም ከፍጹምነት ደረጃ ይደርሳሉ።እነዚህም የመንፈሳዊነት ሦስቱ ደረጃዎች ወጣኒነት፣ ማዕከላዊነት፣ፍጹምነት በመባል በስም የሚታወቁ ሲሆን በተግባር ግን ንፅሐ ሥጋ፣ንፅሐ ነፍስ፣ ንፅሐ ልቦና ይባላል።

ቅዱሳን ደረጃ በደረጃ የሚደርሱባቸው አሥር ማዕረጋት ሦስቱ በንፅሐ ሥጋ አራቱ በንፅሐ ነፍስ ሦስቱ በንፅሐ ልቡና የሚመደቡ ናቸው።

5.1.<u>ንፅሐ ሥጋ ወጣኒነት</u>

ይህ ደረጃ ወጣኒነት በባሕርዩ ፍጹም ከሆነው እግዚአብሔር ፍጹም ጸጋን ተቀብለው ለመክበር ቁርጥ ተጋድሎ የሚጀምሩበት ሕይወት ነው።በዚህም ጊዜ ጠላት ዲያብሎስ ተስፋ የሚያስቆርጥ እና የሚያዳክም ልዩ ልዩ ፈተና በማምጣት ይዋጋቸዋል።እነርሱ ግን በፍጹም ተጋድሎ በእግዚአብሔር ጸጋ ከአንዱ መዓርግ ወደ ሌላው ይሸጋገራሉ።በዚህ ደረጃ ያሉት ሦስት መዓርጋት የሚከተሉት ናቸው።

5.1.1.<u>ጽማዌ</u>

ጽማዌ ማለት፣ዝምታ፣በጸጥታ ውስጥ መኖር፣መናገር መቀባጠርን መተው ማለት ነው።በቃል ብዛት ውስጥ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም ከንፈሩን የሚገታ ግን አስተዋይ ነው።ምሳ 10፥19 እንዲል ዝምታ ማብዛት ነው።

ይህን የመጀመሪያውን ደረጃ በዝምታ ለማለፍም አንደበት እሳት ነው።አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል።

ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና የፍጥረትንም ሩጫ ሁሉ ያቃጥላል በገሃነምም ይቃጠላል።ያዕ 3፥6-12።ከሚለው ፍርድ መዳን ነው።ጌታም በወንጌል ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ ከቃልህ የተነሣ ትኮነናለህ ብሏል።ማቴ 12፥37።ጠቢቡ ሰሎሞንም ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው። የሚወዱአትም ፍሬዋን ይበላሉ በማለት ተናግሮአል።ምሳ18፥21።

በዚህ ማዕረግ ያሉ ቅዱሳን መላእክትን ሲወጡና ሲወርዱ ይመለከታሉ።ነገር ግን ለምን እንደሚወጡና እንደሚወርዱ አያውቁም <u>ለምሳሌ</u>፥ዮሐንስ ሐጺር የሠራውን እንቅብ ለመሸጥ ገበያ ተቀምጦ በነበረበት ሰዓት በተመስጦ ቅዱስ ሚካኤልንና ቅዱስ ገብርኤልን ሌሎችንም መላእክት በየማዕረጋቸው ሲወጡና ሲወርዱ እያየ ያደንቃል።በዚህ ጊዜ እንቅብ መግዛት የፈለገ ሰው ባለ እንቅብ (ስፌት) ዋጋ ንገር ቢለው “ሚካኤልኑ የግቢ ወሚመ ገብርኤል- ሚካኤል ነው የሚበልጠው ወይስ ገብርኤል” በማለት እርሱ የሚያየውን የሚያይ መስሎት ጠይቋል። ዓለማውያንና መንፈሳውያን የሚያስቡትና የሚያዩት የተለያየ ነውና ሰውየውም ይህስ ዕብድ ነው።ብሎ ትቶት ሄዷል የቅድስት አትናስያስም ታሪክ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው።

5.1.2.<u>ልባዌ</u>

ልባዌ ማለት፣ልብ ማድረግ፣ማስተዋል ማለት ነው።ከዚህ መዓርግ የደረሱ ቅዱሳን መላእክትን ሲወጡና ሲወርዱ ሲላላኩ ማየት ብቻ ሳይሆን ለምን እንደሚወጡና እንደሚወርዱ ምክንያቱንም ያውቃሉ ማለት ነው።ጌታ በወንጌል መስማትን ትሰማላችሁ ነገር ግን አታስተውሉም በማለት የተናገረው ልባዊ (ማስተዋል) ታላቅ ማዕረግ በመሆኑ ነው።ማቴ 13፥14። ደቀ መዛሙርቱንም አስተዋላችሁን እያለ ይጠይቃቸው ነበር።ማቴ 13፥51።

5.1.3.<u>ጣዕመ ዝማሬ</u>

ጣዕመ ዝማሬ ማለት የሚጸልዩትን ጸሎትና የሚያመሰግኑትን ምስጋና ምሥጢሩንና ትርጉሙን አንድ በአንድ ማወቅ ያንኑ ምስጋና ጸሎት ያለመሰልቸት መጸለይና ማመስገን ነው። ቅዱሳን የሚጸልዩትና የሚያመሰግኑት ምስጋናና ጸሎት ቢውለበትና ቢያድሩበት አይሳለቻቸውም።ምክንያቱም ምሥጢሩ እየገባቸውና እየተረዳቸው ስለሚያደርጉት ነው። እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና በማስተዋል ዘምሩ እንደ ተባለ።መዝ 46፥7።

ከጣዕመ ዝማሬ የደረሰ አንድ ባሕታዊ ለብዙ ዘመናት ያህል “አቡነ ዘበሰማያት” ብቻ እያለ ያንኑ ምስጋና እያመላለሰ “ይትቀደስ ስምከ” ሳይል ኖረ መልዓክ እግዚአብሔር ተገልጦ ይትቀደስ ስምከ” በል እንጂ ቢለው እኔስ አባታችን ሆይ የሚለው ኃይለ ቃል ምሥጢሩንና ጣዕሙ በአፌ እንደ ጨው እየሟሟ አላጠግበኝ ብሎአል እንዴት አድርጌ ወደፊት ልሂድና “ስምህ ይቀደስ” ልበል በማለት መልሶለታል።

አንድ ሰው የሚጸልየው ጸሎትና የሚያመሰግነው ምስጋና በትርጓሜና በምሥጢር በውስጣዊ ልቡናው እያደመጠ የሚያደርሰው ከሆነ ተመስጦውን ገንዘብ ማድረግ ይቻለዋል።ጸጋ መንፈስ ቅዱስንም እየተጐናጸፈ ከዚህ ከሥጋዊው ነገር በሙሉ ያመልጣል።ለዚህም ነው ንጽሐ ሥጋን በሦስቱ መዓርጋት ገንዘብ ማድረግ የሚቻለው።

ቅዱስ ያሬድ እግዚአብሔር የገለጠለትን ሰማያዊ ዜማ በሚያዜምበትና በመቋሚያው በሚዘምምበት ጊዜ ንጉሡ አጼ ገብረ መስቀል የቅዱስ ረድኤት አድሮባቸው በተመስጦ ይሰሙት ነበር።ሳያውቁትም (ሳያስቡት) በያዙት በትረ መስቀላቸው እግሩን ይወጉታል።ይህ ሁሉ ሲሆንና ደሙ ሲፈስ ለቅዱስ ያሬድ አልተሰማውም።

ለመጸለይና ለማመስገን የምንሳንፍና የጸለይነውን ጸሎት ለመድገም የምንሰለች ቶሎ ቶሎ ብለን ንባቡን ለመጨረስ የምንቸኩል ከሆነ ከዚህ ጸጋ ሁሉ በታች መሆናችንን ልናውቅና ድክመታችንን ልናስተከክ ይገባል።

5.2. ንጽሐ ነፍስ

ንጽሐ ሥጋን ገንዘብ ያደረጉ ሰዎች ቀጥለው የሚሸጋገሩት ወደ ንጽሐ ነፍስ ነው።በንጽሐ ነፍስ የሚገኙት አራት ማዕረጋት ናቸው።እነርሱም፡-

5.2.1.አንብዕ

አንብዕ ማለት እንባ ማለት ነው።ሰው በደረሰበት ኃዘን ልቡ ተወግቶ ፊቱ ተከፍቶ የሚያለቅሰው ለቅሶ አለ ደስታ ሲያጋጥመው ልቡናው በሐሴት ተምልቶ ስሜቱን መቆጣጠር አቅቶት የሚያነባው እንባ አለ አንብእ ከዚህ ይለያል።

ቅዱሳን ሰውነታቸው በኃዘን ሳይከፋ በሥጋዊ ሐሴት ሳይሞላ ሳይሰቀቁ ከዓይናቸው የሚያፈልቁት እንባ ነው።የሚያስቡትም

- ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል የተቀበለውን መከራ
- ሰማዕታት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሉ የተቀበሉትን መከራ
- ጻድቃን ከአጋንንትና ከእኩያት ፍትወታት ጋር ያደረጉትን ተጋድሎ

የራስንና የሌላውን ኃጢአት እያሰቡ ማልቀስ ነው።ክቡር ዳዊት በእንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ።መዝ 6፥6 እንዳለ ከዓይናቸው የሚፈሰው እንባ ሰሌን እስከ ማራስ እንደደረሰና ዜና ሕይወታቸው ይናገራል።

ለምሳሌ፡-አርሳንዮስ ሁልጊዜ ከማልቀሱ የተነሣ ሰሌን ያርስ ነበር።ይህንንም በማድረጋቸው "ብፁዓን እለ ይለህው ይእዜ እስመ እሙንቱ ይትፌሥሑ ዛሬ የሚያለቅሱ ብፅዓን ናቸው። መንግሥተ ሰማያትን በመውረስ ይደሰታሉ ተብሎላቸዋል"።ማቴ 5፥4።

5.2.2.ኩነኔ

በማዕርጋት ሂደትና ስያሜ ኩነኔ ማለት ሥጋን ለነፍስ ማስገዛት ማለት ነው።ሥጋና ነፍስ ሁል ጊዜ ፍላጎታቸውና አካሄዳቸው ስለማይስማማ አንዱ በሌላው ላይ እንደተነሣሣ

ይኖራል። ሥጋ መብላት፣መጠጣት፣መጫወት፣ማረፍ፣መዝናናት የመሳሰለውን ሲወድ ነፍስ ደግሞ ጸምን፣ጸሎትን፣ትጋትን፣ንጽሕናን እና የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ሥራ ትወድዳለች።በዚህም በሥጋና በነፍስ ጦርነት ይካሄዳል።ገላ 5÷16።

ቅዱሳን ከኩነኔ ማዕረግ ሲደርሱ ፈቃደ ሥጋቸው ፈጽሞ ለፈቃደ ነፍሳቸው ያለ ተቃውሞ ይገዛል።ሥጋ የነፍስ መሣሪያ ይሆናል።ነፍስ የወደዳቸውና የተመኘችውን መልካም ነገር ሁሉ ሥጋ ትሰራዋለች።መጸም፣መጸለይ፣መስገድን ሁሉ ይታዘዛል።የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ስቀሉ የተባለው ከዚህ አንጻር ነው።ገላ 5÷24።

ሥጋ ለነፍስ ተገዛ ማለት እንስሳዊ ባሕርዩ ደከመ ለመልዓካዊ ባሕርይ ተሸነፈ መልዓካዊ ባሕርይ ሰለጠነ ማለት ነው።በዚህ ጊዜ ፍጥረታዊ ሰው ሊሠራው ቀርቶ ሊሰማው የሚከብድ እና የሚደንቅ ሥራ ይሠራሉ።በቀን በብዙ ሺህ የሚቆጠር ስግደት ይሰግዳሉ ሥጋዊ ምግብ ብዙ ጊዜ ሳያስፈልጋቸው ይኖራሉ።እንቅልፍ ከዓይናቸው ይጠፋል በትጋሃ ሌሊት ያድራሉ መዝ 131÷4።

5.2.3. <u>ፍቅር</u>

"ፍቅር" ማለት እግዚአብሔር ከመፍጠር ያልናቀውን ፍጥረት ሁሉንም አስተካክሎ መውደድ ነው።

- ኃጥእና ጻድቅ
- አማኒና መናፍቅ
- ጠላትና ወዳጅ ብሎ መለያየት ሳይኖር ማንኛውንም ሰው በእግዚአብሔር አርዓያና አምሳል የተፈጠረውን ሰው መውደድ ነው።የሚወዱትን መውደድ እንኳን የቅዱሳን መገለጫ ይቅርና ክርስቲያናዊ ፍቅር እንዳልሆነ እንኳ የሚወድዷችሁን ብቻ ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ ቀራጮችስ ያኑ ያደርጉ የለምን ተብሎአልና።ማቴ 5÷47።

እውነተኛ ፍቅር ግን፦

- ለሚያሳድዱት ይጸልያል
- የሚረግሙትን ይባርካል

ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ ለሚወግሩት ሰዎች ጌታዬ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ የጸለየው የፍቅር ማዕረግ ስለደረሰ ነው።ሐዋ 7፥60።

5.2.4. <u>ሑሰት</u>

ሑሰት ማለት ካለበት ቦታ ሁኖ ካሰቡበት ቦታ መድረስ ነው።ይህም ማለት ፀሐይ ከአንድ ቦታ ላይ ሁና ብርሃኗ ከሁሉም ቦታ እንደሚደርሰው ማለት ነው።ቅዱሳን ከዚህ ደረጃ ሲደርሱ ከቦታቸው ሁነው በሌላው አገር የሚሠራውን በጸጋ እግዚብሔር ያውቃሉ።ለምሳሌ፦ የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ

የአሦር ንጉሥ ወልደ አዴር በቤተ መንግሥቱ ሁኖ የመከረውን 2 ነገ 6፥8-12፣31፥33

ቅዱስ ጴጥሮስ፦ሐናንያንና ሰጲራ የደረጉትን ክፉ ሥራ ማንም ሳይነግረው ከቤቱ ሁኖ እንዳወቀው።ሐዋ 5፥1-11።

5.3. <u>ንጽሐ ልቡና</u>

ወጣኒነትንና ማዕከላዊነትን ተመልክተናል ንጽሐ ልቡና የመጨረሻው ደረጃ ነው።ከንጽሐ ነፍስ የደረሱት ሊያመልጡትና ወደ ፍጹምነት ማዕረግ ሊደርሱ ስለሆነ ዲያብሎስ ኃይሉን በሙሉ አሟጦ በመጠቀም ይዋጋቸዋል።በዚህ ጊዜ በገሃድ ተገልጦ ይዋጋል።በመጀመሪያና በሁለተኛው ዘንድ እባብ አንበሳ ነብር እየሆነ በመምጣት ለማስፈራራት ይሞክራልሽፍታ እየመሰለ መደባደብ ሁሉ ይጀምራል።

በዚህ ጊዜ በመዝሙር 90፥1፣መዝ 22፥1 ያለውን በመዝሙርና በመጸለይ ድል ይነሡታል። ይህን ሁሉ መከራ በርትቶ ያሸነፈ በእግዚአብሔር ኃይል ወደ ፍጹምነት ማዕረግ ይደርሳል። “ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል፣ያድናችሁማል፣ያበረታችሁማል፣” እንደተባለ።1ጴጥ 5፥10።

የመጨረሻዎቹ የፍጹምነት ማዕርጋት የሚከተሉት ናቸው።

5.3.1. <u>ንጻሬ መላእክት</u>

ቅዱሳን ሰዎች በንጻሬ መላእክት ማዕረግ በጸዐደ ሥጋ ሆነው ቅዱሳን መላእክትን በየከተማቸውና በየቦታቸው ያያሉ ንጻሬ ማየት ማለት ነውና በሦስቱ ዓለመ መላእክት በኢዮር፣ እራማ ኤረር ያሉ ቅዱሳን መላእክትን በየነገዳቸውና በየአለቃቸው እንዲሁም በየክፍላቸው ሁነው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ ያያሉ ይህንን ከማየታቸው የተነሣ ሥጋዊ አኗኗር እየተረሳቸው ስለሚሄድ በዚህ ዓለም እያሉ በዚህ ዓለም የሚደረገውን ድርጊትና ያለውን ውጣ ውረድ ይረሱታል ምክንያቱም ኑሮአቸው ከሰማያውያን ጋር ነውና።

5.3.2.<u>ተሰጥሞ ብርሃን</u>

ተሰጥሞ ብርሃን ማለት በብርሃን ባሕር ሲዋኙ መኖር ነው።ይህ ብርሃን ዓይንን የማይበዘብዝና የማያቃጥል ፍጹም ልዩ ብርሃን ነው።ጨለማ የማይሰለጥንበት የብርሃንም መዓዛና ጣዕም ነፍስን ከሥጋ በመለየት ሚያስደስት ነው።

እነዚህን ጸጋዎች የሚያውቁ ከዚህ ማዕርግ የደረሱ ቅዱሳን ብቻ ናቸው።እኛ በመጻሕፍት ካልሆነ መረዳት አንችልም ይህም እግዚአብሔር ቅዱስ ጳውሎስን የጠራበት መብረቅና ያናገረበትን ድምፅ ይመስላል።ከቅዱስ ጳውሎስ በቀር ከእርሱ ጋር አብረው የነበሩት ሁሉ የመብረቅን ብልጭታውን አላዩም ነጐድጓዱንም አልሰሙም ቅዱስ ጳውሎስን የሚያናግረውን የእግዚአብሔርንም ድምፅ አልሰሙም ሰዎች ይሰሙት የነበረው የጳውሎስን ድምፅ ብቻ ስለነበር ማንን ያናገራል እያሉ ግራ እንደተጋቡ ተመዝግቧልና።ሐዋ 9፥1-8።

5.3.3.<u>ከዊን እሳት</u>

ከዊን እሳት የመጨረሻው ማዕረግ ነው ከዚህ ደረጃ የደረሱ ቅዱሳን ሰውነታቸው አጋንንትን የሚያቃጥል የማያስቀርባቸው ይሆናል ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ከዚህ ማዕረግ በመድረሱ ተሐዋስያን ከሰውነቱ ሲያርፉ እየተኮማተሩ እናእያረሩ ሲወድቁ ቅ/ኤፍሬም ተመልክቷቸዋል

ከዚህ ማዐረግ የደረሱ ቅዱሳን የልብ ንጽሕናና ገንዘብ አድርገዋልና ለነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ ይበቃሉ። “ብፁዓን ንፁሐን ልብ እስመ እሙንቱ ይሬአይዎ ለእግዚአብሔር-ልበ ንጹሐኖች ብፁዓን ናቸውእግዚአብሔርን ያዩታልና። ተብሎ የተጻፈው ይህን ክብር ይመለከታል።ማቴ 5፥8።

ለዚህ መብቃት ታላቅ ብቃትና መዓርግ ነው።በባሕርዩ የሚታይ እግዚአብሔር ለባሕርያቸው በሚስማማ መልኩ በሦስትነትና በአንድነት በቀራኒዮ እንደተሰቀለ በቤተልሄም እንደተወለደ በደብረ ታቦር እንደተገለጠው ሁኖ ይገለጥላቸዋል።

ከንጽሐ ልቡና መዓርግ የደረሱ ቅዱሳን ሥጋዊ አኗኗርና አስተሳሰብ ፈጽሞ ይጠፋላቸዋል።ቅዱስ መቃርስ በአንድ ወቅት ወደ ሌላ ገዳም ሄደህ ቅዱሳንን ጐብኝ የሚል ሃሳብ በተደጋጋሚ በሕሊናው ሲመላለስበት ጸብአ ፍልሰት እንዳይሆን ብሎ አምስት ዓመታት ያህል ታገሠ በኋላ ግን ከእግዚአብሔር መሆኑን ሲረዳ ተነስቶ ሄደ።በጉዞ ላይ እያለ ሁለት ሰዎች ራቁታቸውን በመሆን ከአራዊት ጋር (ድኩላና አጋዘን) ወደ ወንዝ ሲወርዱ አገኘ። እነዚያም ሰዎች መቃርዮስ አይዞህ እኛ መናፍስት አይደለንም ሰዎች ነን በማለት አናገሩት በዚህ ጊዜ መቃርስ እየተደነቀ።

እንዴት ወደዚህ መጣችሁ?

የሌሊቱ ቁርና የቀኑ ሐሩር ሰውነታችሁን እንዴት አልጐዳውም?

ምንስ እየቀመሳችሁ ትኖራላችሁ?በማለት ጠየቃቸው እነርሱም በባሕር ላይ ያለውን አረንጓዴ ነገር ነፍሳችን ከወደደች ትበላዋለች ባትወደው ደግሞ ትተወዋለች።

ከበርዱና ከሐሩሩም እግዚአብሔር እየጠበቀን አለን ብለው መለሱለት።በመቀጠልም መቃርስን

- በዓለም ላይ እንደቀድሞው ፀሐይ ትወጣለች?
- ጳጳሳትና ንጉሥ ይሾማል?በማለት ጠየቁት

ከዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባው በዚህ ዓለም እየኖሩ ይህን ዓለም የረሱት መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም ከዓለም ተለይተው ሕይወታቸው ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና።ቈላ3÷1-4።

ቅዱስ ጳውሎስ “እኔ ለዓለም የሞትኩ ነኝ ዓለምም በእኔ ዘንድ የሞተች ናት” ማለቱ ተጋድሎውን እስኪፈጽም ድረስ በዚህ ዓለም ቢኖርም የዓለምን ሥራ አልሠራም ዓለም በእርሱ ላይ የሠራችውና የሰለጠነችበት አንዳች ነገር የላትም ሁለቱ የተለያዩ ነበሩ።ገላ 6÷24።በዚህ ዓለም በነበረ ሕይወቱም የሚኖረው እርሱ ሳይሆን ክርስቶስ መሆኑን ሲገልጽ

“ከክርስቶስ ተሰቅያለሁ እኔም አሁን ሕያው ሁኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል”።በማለት ነው።ቅዱሳንም ከዚህ ዓም ነገር ፈጽመው የተለዩ ናቸው።

- የሥላሴን ምሥጢርና ህልውና ሲያደንቁ
- በረቂቅ ብርሃን ሲመላለሱ
- የመላእክት ምስጋናና ቅዳሴ ሲመለከቱ የሚኖሩ ስለሆነ ይህን ዓለም የሚያስቡበት ጊዜና ሕሊና የላቸውም ትልቁን የፀሐይ ወይም የአምፖል ብርሃን ያገኘ ሰው የሻማ ብርሃን እንደሚያስፈልገው።

ሰው ሁሉ ከዚህ ፍጹም ጸጋ ተካፋይ ይሆን ዘንድ ቅዱስ ጳውሎስ “ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቀቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ” በማለት ጥሪውን አስተላልፏልና ወደ ጸጋው ዙፋን አሁኑኑ በእምነት እንቅረብ።

እግዚአብሔር በማይነገር ቸርነቱ እርሱን ፈልገው ጸጋውን ሽተው መከራን ለታገሡና ጊዜያዊና ኃላፊ ደስታን ለናቁ ወዳጆቹ ያዘጋጀው የሀብቱ መጠን እጅግ ብዙ ነው ዮሐ 14÷3።

የአሥሩን መዓርጋት ጣዕምና ጸጋ እንኳንስ ምግባር ሠርቶ ከጸጋው ወገን አንዱን ላልቀመሰ ይቅርና ጸጋውን ይዘውት ላሉት ለራሳቸው ለቅዱሳንም ቢሆን በአንደበት አከናውኖ ለመናገር የሚያስቸግር ዕፁብ ድንቅ ነው። “የእግዚአብሔር ባለ ጸግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው”እንደተባለ።ሮሜ 11÷33።

እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጥቆ ረቂቅ ምሥጢር ማየቱን ቅዱስ ጳውሎስ ተናገሯል። በዚያ የተመለከተውን ሲገልጽ ግን ሰው ሊናገረው የማይገባውን የማይናገረውን ቃል ሰማ በማለት ምሥጢሩን ከሰው እውቀትና ሕሊና በላይ እንደሆነ አስረድቷል።2ቆሮ 12÷3-5።

ምዕራፍ ስድስት

የቅዱሳን ቃል ኪዳን ከነገረ ድኅነት አንጻር

“ነገረ ድኅነት”የሚለው ትምህርት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሞት የተገኘውን የመዳን ትምህርት ያጠቃልላል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ ድኅነቶች ተገልጸው እናገኛለን።

- ኖኅም ቤተሰቡ ከጥፋት ውኃ መዳናቸው
- እስራኤል ከግብፅ ባርነት ነፃ መውጣታቸው
- ኢየሩሳሌም አሥራውያን ካዘኃጁት ጥፋት መዳናቸው
- ሶሪያዊው ንዕማን ከለምጽ በሽታው በዮርዲያኖስ ወንዝ መዳኑ
- ኢዮብ ከነበረበት ደዌ ሁለ መዳኑ

ይሁንና እነዚህ ድኅነቶች ጊዜያዊና በዚህ ዓለም ብቻ የተወሰኑ ነበር።ይህም ማለት መሠረታዊ ችግሮችን ያልፈታ፣ሰውን ከተፈረደበት የዘለዓለም ቅጣት (ሞት) ያላዳነ፣ የተዘጋውን ገነት ያላስከፈተ ነበር።

ድኅነት ማለት በኃጢአት ምክንያት የወደቀውን ባሕርዩ የጐሰቆለው የሰው ልጅ ከደረሰበት ድቀትና ሞት ሙሉ በሙሉ ነፃ መውጣቱንና አጥንቶች የነበረውን ጸጋ ማግኘቱን፣ መጀመሪያ ወደ ነበረበት ሕይወት መመለሱን የሚገልጥ ነው።ይህም የተከናወነው ሰው ሁኖ በተገለጠው በእግዚአብሔር ልጅ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የመዳን ትምህርት የቤተ ክርስቲያን መሠረትና የማይናወጥ የማዕዘን ድንጋይ ነው። በአዲስ ኪዳን ማንኛውም አሳብና አስተምህሮ የሚመዘነውና የሚለካው በነገረ ድኅነት ትምህርት ነው።የቅዱሳን ቃል ኪዳንም የሚታየው ከዚህ አስተምህሮ አኳያ ነው።ስለሆነም የቅዱሳን ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠው የቸርነት ሥራ ድልድይ ሁኖ የሚያገለግል ነው።

የቅዱሳን ቃል ኪዳን የሚጠቅመው አንድ ሰው በሃይማኖት እየኖረ የሚቻለውን ያህል ምግባርና ትሩፋት እየሠራ ከዚያ ለሚቀረውና ለሚሳሳተው አምላኩ እግዚአብሔርን የቅዱሳኑን ስም በማስታወስ ቢለምነው ስለ ወዳጆቹ ሲል ምሕረት ሊያደርግለት ይችላል። በመሆኑም በቅዱሳን ቃል ኪዳን መጠቀም የሚቻለው ሕጉንና ትዕዛዙን በመጠበቅ ጥንቃቄ በተሞላበት ሕይወት እየኖሩ ለምንሳሳተውና በንስሐ ደጅ ለምንጠናው እንዲያግዘን እንጂ ከክርስቲያናዊ ስነ ምግባር ውጪ በሆነ ሕይወት እየኖርን ራሱን ወክሎ (ችሎ) ሃይማኖትና ምግባር እንዲሆን አይደለም።

6.1.<u>የቃል ኪዳን ምንነትና አመሠራረት</u>

6.1.1. <u>የቃል ኪዳን ትርጉም</u>

“ቃል ኪዳን” የሚለው ሐረግ “ኪዳን” ተካየደ፣ተማማለ፣ቃል ተገባባ ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ነው። “ኪዳን” የሚለው “ቃል” ከሚለው ጋር ተገናኝቶ “ቃል ኪዳን” የሚለውን ሐረግ ይሰጣል።

ቃል ኪዳን በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው። በስምምነቱ በሚካተቱ በሁሉም ወገኖች እያንዳንዳቸው የሚጠበቅባቸውንና ሊያደርጉት የሚገባቸውን ተግባር በግልጽ የሚያሳይና የሚገልጽ ውል ነው።

ቃል ኪዳን የሚገቡ ወገኖች የቃል ኪዳን ምልክትና የቃል ኪዳን ማጽኛ ያስቀምጣሉ። በመሐላ፣በመፈራረም፣የሰዎች ምስክር በማቆም፣ሐውልት በመትከልና በመሳሰሉት ሊሆን ይችላል።

ቃል ኪዳን ከተራ ውሎችና ስምምነቶች የበለጠ ጽኑና ቋሚ ነው።ከፍ ያለ ክብደትም አለው አንድ ቃል ኪዳን ለማፍረስ የሁለም ወገኖች ቃል የተግባቡት ስምምነት ያስፈልጋል።አለበለዚያ አንዱ ወገን ብቻ ቢያፈርስ ሕግ አፍራሽ ይሆናል።የቃል ኪዳኑ ስምምነት በውስጡ ያሉትን አካላት እንደ ሕግ ሁኖ ይገዛቸዋልና።

6.1.2.ቃልኪዳን ለምን አስፈለገ?

በስምምነቶች መካከል የቃል ኪዳን ውል ለምን ያስፈልጋል? የቃል ኪዳን ውል የሚያስፈልገው ከተለያዩ ምክንያቶች አንጻር ነው።

ሀ.ለቃል ኪዳኑ ተቀባዮች ተስፋው የተፈጸመ እንዲሆን፦ ወደፊት ያለና ያልተደረሰበትን ነገር ተስፋ ለማድረግ የተስፋው መያዣና ተስፋው አማናዊ እንዲሆን በቃል ኪዳኑ ልቡና ተረጋግቶ ማረፍ እንዲችል ነው።ምንም መጨበጫ የሌለውንና በባዶ ተስፋ የተሞላውን ነገር ለመቀበል ስለሚቸግር ነው።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስን መያዣ ሰጠን።2ቆሮ 5፥5።ያለው ለዚሁ ነው።

አንድ ሰው አንድን ነገር ሊገዛው ሲፈልግ ቢያንስ የተወሰነ የቅድሚያ ክፍያ ይከፍላል። በዚህም ዕቃውን ለሚፈልጉና ለመግዛቱ ቀሪውንም ለመክፈሉ ማስተማመኛና ማስረጃ ይሆናል። እንደዚሁ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም የሰጠን መያዣ በሚመጣው ዓለም ይሰጠን ዘንድ ተስፋ ያስደረገንን ሁሉ በእውነት እንደሚሰጠን ማረጋገጫ ነው።በዚህ ዓለም የሰጠን የተስፋው መያዣዎችም

1.በጥምቀት ልጅነትን ማግኘታችን ለመንግሥቱ ወራሽነት

2.ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መስጠቱ ከእርሱ ጋር ተዋሕደን ለምንኖረው ዘላለማዊ ሕይወት

3.ከእርሱ ጋር ስንኖር የምናገኘው ደስታ ለዘላለም ደስታ

4.ከእርሱ ጋር መታረቃችን ለመዳናችን ሮሜ 5፥10።

5.የባሕርይ ልጁን ለእኛ ሕይወቱ አሳልፎ መስጠቱ ሁሉን ነገር የሚሰጠን ለመሆኑ።ሮሜ 8፥32 መያዣዎችና ማስተማመኛዎች ናቸው።

6.1.3.በቃል ኪዳን መካተት ያለባቸው

የቃል ኪዳን አካል የሆኑት ሁሉ ከመስማማታቸውና ወደ ቃል ኪዳን ከመግባታቸው በፊት ከምንም ነገር ነፃ ናቸው።ከቃል ኪዳን በኋላ ግን እያንዳንዱ የቃል ኪዳን አካል በቃል ኪዳኑ የተገለጹለትን ነገሮች የማድረግ ግዴታ ውስጥ ይገባል ቃል ኪዳን የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች ያካትታል

ሀ.ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የሚደራደሩ አካላት መኖር

ለ.ወደ ቃል ኪዳን ለመግባት ምክንያትና ዓላማ መኖር

ሐ.ቃል ኪዳኑን በነፃ ፈቃድ ለመጠበቅ መወሰን

መ.ቃል ኪዳኑን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ውጤት ማወቅ

6.1.4.የቃል ኪዳን ዓይነቶች

ቃል ኪዳን ማኅበራዊና በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የተደረገ ተብሎ በሁለት መንገድ ሊከፈል ይችላል።

ሀ.ማኅበራዊ ቃል ኪዳን፡- ይህ ዓይነት ቃል ኪዳን፡-

- በጓደኞች መካከል 1ሳሙ 20፥3፣16፥17
- በባልና ሚስት መካከል
- በመንግሥታት መካከል 1ነገ 5፥12
- በአሠሪና ሠራተኞች መካከል
- በሥራ ባልደረቦች መካከል የሚደረግ ነው
- በቤተሰብ መካከል የሚደረግ ዘፍ 31፥43-54

ለ.በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የተደረገ ቃል ኪዳን፡- በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ቃል ኪዳን በአሰጣጡ በሁለት ይከፈላል

1.ለሁሉም የሰው ልጅ የተሰጠ ቃል ኪዳን

2.በመታዘዝ ላይ (በሥራ) የተሰጠ ቃል ኪዳን ናቸው።

ለሁሉም የሰው ልጅ የተሰጠ ቃል ኪዳን፦

ይህ ቃል ኪዳን በሰው አማካኝነትም የተሰጠ ይሁን በቀጥታ እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን የሚያስተዳድርበት ቃል ኪዳን ነው።ይህም በሰው መታዘዝ ላይ ያልተመሠረተ ነው።

1.ሥነ ፍጥረታዊ ቃል ኪዳን

ሥነ ፍጥረት በተፈጠረበት ዓላማና ሥራ ጸንቶ መኖር ሥነ ፍጥረት በታወቀና በተወሰነ ሕግ በቃል ኪዳን ሥርዓት መተዳደሩ የሰውን የኑሮ ሕይወት ቀላል ያደርገዋል።መቼ?ምን ይመጣ ይሆን? በማለት እንዳይጨነቅ ያደርገዋል።

- የቀንና የሌሊት
- የብርሃንና የጨለማ
- የክረምትና የበጋ
- የሙቀትና የብርድ
- የየዕለቱ የአየር ንብረት
- የእንሰሳትና የአራዊት ሁኔታ ስምምነታቸው ሥነ ፍጥረታዊ ቃል ኪዳን ነው።

2.ከኖኅ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን

በሰው ልጅ ኃጢአት ምክንያት ፍጥረት በጥፋት ውኃ ጠፍቷል።ሁለተኛ ላለማጥፋት ግን እግዚአብሔር በኖኅ አማካኝነት ቃል ኪዳን ገብቷል።በዚያ ቃል ኪዳንም ምንም እንኳ ዓለም በክፉ ኃጢአት ውስጥ ቢገኝም እግዚአብሔር ዓለምን አያጠፋም።ዘፍ 9፥2-17።

በመታዘዝ ላይ (በሥራ) የተሰጠ ቃል ኪዳን

ይህ ዓይነቱ ቃል ኪዳን በቃል ኪዳኑ ተቀባይ ሊፈጸም የሚገባው ግዴታና ትዕዛዝ ያለበት ቃል ኪዳን ነው።በቃል ኪዳኑ ለመጠቀም ሰው የታዘዘውን ሲፈጽምና ሲያደርግ በዚያ የተገለጸውን ተስፋና ዋጋ ያገኛል።ከእርሱ የሚጠበቀውንና የሚፈለገውን ካልፈጸመ ግን በቃል ኪዳኑ የተነገረውን ተስፋና ዋጋ አያገኝም።ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፦

1.ኪዳነ አብርሃም

አብርሃም በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ከአገሩና ከወገኑ ተለይቶ ሁሉን ነገር ትቶ ሂድ ወደተባለው አገር ከመሄዱ የተነሣ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ በመገለጥ፡-

- የምድር ወገኖች በዘሩ እንደሚባረኩ
- የሚባረኩት እንዲባረኩ፣የሚረገሙት እንደሚረገሙ
- ዘሩ እንደሰማይ ክዋክብትና እንደምድር አሸዋ እንደሚበዛ
- ዘሩ የተስፋይቱን ምድር እንደሚወርስ ቃል ኪዳን ገባለት ይህም የተስፋው መያዣ የሆነ ግዝረትን ምልክት አድርጎ ሰጠው እግዚአብሔርም ይህንን ሁሉ አደረገ።

2. ኪዳነ እስራኤል

እግዚአብሔር ግብጻውያንን ከመታና ሕዝቡን ነፃ ካወጣ በኋላ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ።ሕዝቡ ከግብፅ መውጣታቸውን የሚያስቡበትና የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራና ቸርነት ለልጆቻቸው የሚነግሩበት የፋሲካን መሥዋዕትና በዓል አዘጋጀ።ዘጸ 2፥24-48።ከሕዝቡ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳንም

2.1.እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ፣የእስራኤል ነፃ አውጪና መሪ ጠባቂና ተንከባካቢ መሆኑን አወጀ

2.2.ቃል ኪዳኔን ጠብቁ የሚል ሁሉን አቀፍ የሆነ ትዕዛዝ ሰጠ

2.3.ሕዝቡ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲቀድሱ ታዘዙ

2.4.ሙሴ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል መልእክተኛ መሆኑ ተረጋገጠ

የቃል ኪዳኑ ማረጋገጫ የሆነ አሥርቱ ቃላት የተጻፉበት ጽላትም በእግዚአብሔር ተሰጠ። ነገር ግን እስራኤል ለቃል ኪዳኑ ታማኞች ሁነው አልተገኙም።በዚህም እግዚአብሔር በእነርሱ አልተደሰተም ቃል ኪዳኑን በማፍረሳቸውም ብዙዎቹ በመንገድ ላይ ቀርተዋል።

3. ኪዳነ ዳዊት

እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እኔ ከአንተ ጋር ነኝ በማለት

- ታላቅና ገናና እንደሚሆን
- ድል ማድረግንና ኃይልን እንደሚሰጠው
- ዘሩና መንግሥቱ ጸንቶ እንደሚኖር ቃል ገባለት።

እግዚአብሔር በእውነት ማለ፤አይጸጸትም፤እንዲህ ብሎ፦

“ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ ልጆችህ ኪዳኔን ይህንንም የማስተምራቸውን ምስክሬን ቢጠብቁ ልጆቻቸው ደግሞ በዙፋንህ ላይ ለዘለዓለም ይቀመጣሉ።”መዝ 131፥11።

የዳዊት ልጅ ሰሎሞን እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ላደረገው ቃል ኪዳን ያለውን ታዛዥነትና ታማኝነት በነገሠ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ላይ አሳየ።የቃል ኪዳኑ ተስፋ ቋሚ መገለጫ የሆነውን ቤተ መቅደስም ሠራ።ሆኖም ብዙ ነውር የሆኑ ነገሮችን በማድረግ ቃል ኪዳኑን አፈረሰ።ልጅ ሮብዓምም ምክንያተኛ በመሆን የዳዊት መንግሥት ከሁለት እንዲከፈል አደረገ።

4. <u>ሐዲስ ኪዳን</u>

ለአዳም ከተሰጠው የመጀመሪያ ቃል ኪዳን ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ ለተለያዩ አበው የተሰጡ ቃል ኪዳኖች ሁሉ የሚያመለክቱት ለጊዜው ከተነገሩትና በውስጣቸው ከተካተቱት ነገሮች ጋር አማናዊ ሆነው የሚፈጽሙት በክርስቶስ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት በየኪዳናቱ ውስጥ በተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ታትሞ ተፈጽሞ አዲስ ኪዳን ተሠራ።

የቃል ኪዳኑ መነሻ የራሱ የእግዚአብሔር ቸርነትና ለሰው ያለው የማይለወጥ ፍቅር ነው። የሰውና የእግዚአብሔርን የመልካም ኪዳን ግንኙነት ኃጢአት በመካከል እየገባ ቢያበላሸውም እግዚአብሔር ግን ለሰው ያለውን መልካም አሳብና ፍቅር አልለወጠውም ይህን የእግዚአብሔር ፍጹም ባሕርያዊ ፍቅር የተረዱ ቅዱሳንም ያድናቸው ዘንድ አብዝተው ጩኸዋል።ለምሳሌ ያህል፦ኢሳ 64፥1-12።ያለውን መመልከት ነገራችንን የተረዳ ያደርገዋል።

አዲስ ኪዳን የተሠራው የተመሠረተው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ቃል ኪዳኑ የጸናውም የተስፋው መያዣ አድርጐ በሰጠን በደሙ መሥዋዕትነት ነው።ማቴ 26፥28፣ዕብ 9፥12።

አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ውስጥ በትንቢትና በምሳሌ ታዝሎ በተስፋ ተሰውሮ የኖረ ነበር።ጊዜው ሲደርስ ጌታችን በሥጋው መቆረስ በደሙ መፍሰስ ከሚያምኑና ይህን ከሚቀበሉ ሁሉ ጋር የሕይወትና የይቅርታ ቃል ኪዳን አደረገ።በዚህም ቃል ኪዳን መሠረት በቤዛነቱ አምኖ ቅዱስ ሥጋውን የሚበላ ክቡር ደሙን የሚጠጣ እስከ መጨረሻው ሕቅታ ድረስም የሚጸና ሁሉ የዚህ ቃል ኪዳን ወራሽ ነው።የቃል ኪዳኑ ፍጻሜም ከክርስቶስ ጋር ተዋሕዶ ዘለዓለማዊ ሕይወትን አግኝቶ ከክርስቶስ ጋር ለዘለዓለም ነግሦ ሕያው ሆኖ በሰማይ መኖር ነው።

6.2.<u>እግዚአብሔር በቅዱሳን ቃል ኪዳን የሚሠጠው ምሕረት</u>

እግዚአብሔር ቸር ነው ቸርነቱም የባሕርይው ነው ለቸርነቱም ወሰን የለውም።እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ስለሆነና ቅዱሳንም ሕያዋን ስለሆኑ ከእርሱ ጋር የሚገባው ቃል ኪዳን ቋሚና ሕያው ነው። “ከመረጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳን አደረግሁ” እንዲል መዝ 88፥3። ለቅዱሳኑ ያለው ፍቅር እውነተኛና ጊዜ የማይሽረው ዘላለማዊ በመሆኑ ስለ እነርሱ ሲል ለሌሎች ምሕረትንና ቸርነትን የሚያደርግ መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት የተመሰከረ ነው።

6.2.1.<u>ለእስራኤል የተደረገ ቸርነት</u>

እስራኤል ምድረ ርስትን ይወርስ ዘንድ ከግብጽ የመከራን የባርነት ሕይወት በታላቅ እጅና በተዘረጋች አንድ ባሕር ከፍሎ በማሻገር ነፃ ከማውጣት ጀምሮ አርባ ዓመት ሙሉ የቸርነት ሥራ የሠራው ስለ መልካም ሥራቸው፣ስለ ቅድስናቸውና ስለ ልባቸውም ቅንነት አለመሆኑን እንዲህ በማለት ገልጦታል።

“ስለ ጽድቁ እወርሳት ዘንድ ወደዚህች ምድር እግዚአብሔር አገባኝ ስትል በልብህ አትናገር። እነዚህን አሕዛብ እግዚአብሔር ከፊትህ ያወጣቸው።ምድራቸውን ትወርስ ዘንድ የምትገባው ስለጽድቅህና ስለ ልብህ ቅንነት አይደለም።ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ በሚያጠፋቸው በእነዚያ ለያዕቆብም የማለላቸውን ቃል ይፈጽም ዘንድ

ነው።እንግዲህ አንተ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነህና አምላክህ እግዚአብሔር ይህቺን መልካም ምድር ርስት አድርጐ ይሰጥህ ዘንድ ስለ ጽድቅህ እንዳይደለ እወቅ።ይላል ዘዳ 9፥4-6።

6.2.2. ስለ ዳዊት የኢየሩሳሌም አለመጥፋት

በዘመኑ ኃያልና ገናና የነበረው የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ወደ ሕዝቅያስ "አሁን በእኔ ላይ ያመፅከው በማን ተማምነህ ነው"። በማለት የንቀትና የትዕቢት መልእክት ላከበት።ሕዝቡንም ሕዝቅያስ እግዚአብሔር ያድነናል ብሎ እንዲያታልላችሁ ተጠንቀቁ ብሎ ላከባቸው።ኢሳ 36፥5።

ሰናክሬም ሕያው እግዚአብሔርን ከግዑዛን ፍጥረታት ጋር አንድ አድርጐ በመቁጠሩ ንጉሥ ሕዝቅያስም ወደ እግዚአብሔር በመጸለዩ እግዚአብሔር እንዲህ አለ .....ስለ እኔም ስለ ባሪያዬ ዳዊትም ይህቺን ከተማ አድናት ዘንድ እጋርዳታለሁ።2ነገ 19፥32።

6.2.3.ስለ ዳዊት የእስራኤል መንግሥት አለመከፈል

ቀደም ብለን እንደገለጥነው ሰሎሞን በመጀመሪያ ዘመኑ ብዙ መልካም ሥራዎችን ሠርቶ ነበር።

- የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በልዩ ሁኔታ ሠርቷል
- እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ ተገልጦ አነጋግሮታል
- ሕዝቡን ማስተዳደር የሚችልበት ጥበብ እንዲሰጠው ጠይቋል
- ጥበብን ተጠቅሞ ፍትሐዊ ዳኝነት ሰጥቷል

ሰሎሞን በመጨረሻ ሕይወቱ ግን ከአሕዛብ ሴቶች ጋር በዝሙት በመጠመዱ፣ከአምልኮተ እግዚአብሔር ስለ ወጣ እግዚአብሔር አዝኖበታል።በዚህም ምክንያት መንግሥቱን ለሁለት እንደሚከፈል ተናገረ።ሆኖም ግን ለዳዊት ስለ ገባው ቃል ኪዳን ሲል..... "ዳዊትን እንዳልዋሸው ተናገረ ጊዜ በቅዱስነቴ ማልሁ። ዘሩ ለዘላለም ዙፋኑም በፊቴ እንደ ፀሐይ ይኖራል።ለዘለዓለም እንደ ጨረቃ ይጸናል" ብሎ ስለ ተናገረ የመንግሥት መከፈል ቅጣት በራሱ በሰሎሞን ዘመን ሳይሆን በልጁ ዘመን እንደተፈጸመ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።1ነገ 11፥13፣መዝ 88፥35፣1ነገ 12፥25።

6.2.4.ለቅዱሳን የሚሰጥ ቃል ኪዳን

እግዚአብሔርን በፍጹም ኃይላቸው፣በፍጹም ልባቸውና በፍጹም ነፍሳቸው እስከ ሞት ድረስ ለወደዱና ላገለገሉ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲሉ ፈቃደ ሥጋቸውን በመንፈስ ቅዱስ ሰይፍ የቆረጡ፣ራሳቸውን ለአንድ ክርስቶስ ብቻ ያጡና ያቀረቡ ቅዱሳን የዚህን ዓለም

ጊዜያዊ ተድላና ደስታ ስለ እርሱ ሲሉ እንደተውትና እንደታገሡት ሁሉ እርሱ ደግሞ የዘላለም መታሰቢያ፣ የማይጠፋ ስምና ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል።ኢሳ 56፥3፣ማቴ 10፥40።

ከዚህም በላይ በአንዳንድ ቅዱሳን ገድል ላይ "እስከ አሥርና ሠላሳ ትውልድ ከዚያም በላይ እምርልሃለሁ።"የሚል ቃል ኪዳን እንደ ተሰጣቸው ይናገራል።ይህም ራሱ እግዚአብሔር በደብረ ሲና ለእስራኤል ሕጉን ሲናገር..... "ለሚወድዱኝ ትዕዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነኝና" ብሎ በተናገረው መሠረት ከእርሱ ምሕረትና ቸርነት ጋር የሚስማማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ነው እንጂ ከዚህ ተለይቶ የሚታይና የሚጣላ አይደለም።መታየት ያለበት ዋናው ነገር እግዚአብሔር የሚሰጠው ቃል ኪዳን ምንነትና አፈጻጸም እንጂ የትውልድ ቁጥር ማነስ ወይም መብዛት አይደለም።

ለቅዱሳን የተሰጠ ቃል ኪዳን ለአንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለትውልድ ወይም ለብዙ ዘመናት የሚዘልቅና የሚደረግ በመሆኑ በእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት፣በቅዱሳኑም ቃል ኪዳን ለሚታመን ሁሉ ይደረግለታልና አሥር ሺህና ሠላሳ ሺህ የሚለው ፍጹምነትንም የሚያመለክት እንጂ የቁጥር መንፈስ ብቻ አለመሆኑን ማስተዋል ተገቢ ነው።እግዚአብሔር ለወዳጆቹ አንድ ጊዜ የገባላቸውን ቃል ኪዳን እያሰበ በዚያ ውስጥ የገባውን ቃል ለሚገባቸውና በቃል ኪዳኑ ውስጥ የተካተቱትን ነገሮች ለሚያሟሉ ሁሉ ቸርነቱን ያደርግላቸዋል።

የቅዱሳን ቃል ኪዳን በዓፀደ ሥጋም ሆነ በዓፀደ ንፍስ ሁነው እንደሚሠራ".....በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንዲሁም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና እነዚያ ቀኖችስ በያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ" ተብሎ የተነገረው ስለ ቅዱሳን እንደሆነ መረዳት እንችላለን።ማቴ 24፥21።

<u>ማጠቃለያ</u>፦

"ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፣ያለ እርሱ (ያለ ቅድስና) ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና፣የእግዚአብሔር ጸጋ (የቅድስና ጸጋ) ለማንም እንዳያጐድለው።"ዕብ12፥14 እንዲል።እያንዳንዱ ክርስቲያን በሚኖርበት የክርስትና ሕይወት ስለ ሃይማኖቱ ይጋደል ዘንድ ሐዋርያው ይሁዳ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እመክራችኋለሁ በማለት አስተምሮአል።ይሁዳ 3።አንድ ክርስቲያን በመረጠው የሕይወት መንገድ ፈጣሪውን በማገልገል የቅድስና ተሳታፊና የመንግስተ ሰማያት ወራሽ መሆን ይችላል አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ ብሎ እንዳስተማረን በአንዲት ሃይማኖት የተለያየ ምግባርና ትሩፋት በመሥራት ትወርሳለች።

የሰማዕታት የጻድቃን የባሕታውያን የመነኮሳት የሰበአ ዓለም (የሁሉም ሰው) ሃይማኖትና አጀማመሩ አንድ ነው።ሁሉም ልጅነት የሚያገኘው ከማኅጸነ ዮርዲያኖስ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ነው።የክብሩና የማዕረጉ መለያየት ግን ከሥራና ከምግባር የሚመጣ ነው።ስለዚህ በአንዲት ሃይማኖት ያመነ ሁሉ ባለበት የሕይወት ጉዳና ሁኖ የሚገባውን ከሠራ የቅድስና ተሳታፊ ለመሆን ይችላል።

በአጠቃላይ የቅድስና ሕይወት ልቦናውን ለመንፈስ ቅዱስ ላዘጋጀ ሁሉ የተሰጠ እንደ መሆኑ መጠን ብዙዎች ከተለያየ የኃጢአት ጎዳና ተመልሰው ሕይወታቸው ተቀድሶ ለታላቅ ክብር በቅተዋል።ይህም በእግዚአብሔር ቸርነት የሚፈጸም ነው።እኛም የዚህ ቸርነት ተጠቃሚዎች እንድንሆን የገባነውን ቃል ኪዳንና የተቀበልነውን መስቀል እስከ መጨረሻው እንድንጠብቀውና አገልግለን የአገልግሎታችንን ዋጋ እንድንቀበል ከቅዱሳኑ ጋር በክብር እንዲያቆመን የእግዚአብሔር ቸርነት የቅዱሳን በረከት አይለየን።

ወስበሀት ለእግዚአብሔር

መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ ለይኩን ብርሃኑ

፳፻፯ ዓ.ም